አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂማዩኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ  ፎክሎር ትምህርት ክፍል


# ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ


በ

ደስታ አበጋዝ



ነሀሴ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂማዩኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ  ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በ

ደስታ አበጋዝ


አማርኛ  ቋንቋን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ   ጥናት

ነሀሴ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማረጋገጫ

“ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ” በሚል ርዕስ በደስታ አበጋዝ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

## የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ……………………………..ፊርማ………………ቀን……………………

የውጭ ፈታኝ………………………..ፊርማ………………ቀን……………………

የውስጥ ፈታኝ……………………….ፊርማ………………ቀን……………………

## ማረጋገጫ

"ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂማዩኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም------------------------------------ ፊርማ---------------- ቀን----------------------

በቅድሚያ ሁሉን ላደረገልኝ ለልዑል እግዚአብሄር ምስጋና ይድረሰዉ፡፡

በመቀጠል ለዚህ ጥናት መሳካት ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ ጥናቱ እስከሚጠናቀቅ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከትህትና ጋር በየጊዜው ስህተቶችን በማረም፣ የአሰራር ስልቶችን በመጠቆምና ገንቢ አስተያየትን በመስጠት እንዲሁም በማበረታታት ክትትላቸውና ሙያዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡

የመመረቂያ ጽሁፉን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን በጀት በመመደብ እገዛ ላደረጉልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የትምህርት እድል በማመቻቸት እና ለጥናቱ ስራ የሚያገለግል ገንዘብ በመፍቀድና በመስጠት ድጋፍ ላደረጉልኝ ለትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ለቤተሰቦቼና ለባለቤቴ ለልጆቼ  እንዲሁም በጽሁፍ ላገዘኝ መምህር ጠይሙ ባለንጎን ለመሰግን እወዳለሁ፡፡

## አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2014 ዓ.ም. በ ሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አማካኝነት በታተሙት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰነድ ፍተሻ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆኑ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ እንዲሁም ለደረጃው የተዘጋጁ መርሀ-ትምህርቶች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ ጥናቱም ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ከተነሱ ንድፈ-ሃሳቦች አኳያ በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል፡፡በተተኳሪዎቹ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር በአብዛኛው የሚጣጣሙ መሆናቸውን ከሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች አኳያ ሲፈተሹ በአብዛኛው ግልጽ፣ ትክክለኛ፣ተገቢነትና ተመጣጣኝነት ያላቸው ቢሆኑም አልፎ አልፎ ግን ግልጽነት የጎደላቸው ማብራሪያዎች፣ ትእዛዞች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች፤ ስህተት ያለባቸው የሰዋስው ይዘቶች፤ ከክፍል ደረጃው በላይ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እና ያልተመጣጠኑ ንኡሳን ይዘቶች እንዳሉ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና አደረጃጀት በአብዛኛው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ሲሆኑ አንዳንድ ይዘቶች ግን ምንም ስፋትና ጥልቀታቸው ሳይጨምር የተደገሙ መሆናቸው በደካማ ጎን የሚያይ ነው፡፡ እንዲሁም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን የተከተሉ ቢሆንም በአመዛኙ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ጎልቶ ታይቶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በአብዛኛው በመርሀ-ትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ ቢሆንም የተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ደግሞ በሚገባ መርሀትምህርቱ ላይ ተመስርተው ያለመቅረባቸውን ከተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግም በጥናቱ ማጠናቀቂያ ላይ ክፍተቱን ለመሙላት ያስችላሉ የተባሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

# የይዘት ማውጫ


ምስጋና ....................................................................................................................IV

አህጽሮተ ጥናት ............................................................................................................ II

የይዘት ማውጫ ..............................................................................................................III

ምዕራፍ አንድ ................................................................................................................ 1

መግቢያ ....................................................................................................................... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............................................................................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........................................................................................ 4

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................................................................................................... 5

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................................... 6

1.5 የጥናቱ ወሠን .......................................................................................................... 6

ምዕራፍ ሁለት .............................................................................................................. 7

የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ................................................................................................ 7

2.1. የቋንቋ ሰዋስው ....................................................................................................... 7

2.1.1. የሰዋስው ምንነት ................................................................................................. 7

2.1.3. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት ............................................................................ 9

2.1.4. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ............................................................................... 12

2.1.5.1. ተግባቦታዊ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ COMMUNICATIVE GRAMMAR TEACHING APROACH (CGTA) ........................................................................... 13

2.1.5.2. ተግባር ተኮር አቀራረብ/TASK BASED APPROCH/ ................................ 14

Richards & Rodgers (2001: 151) ስለተግባር ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ሲገልጹ ተግባር ተኮር ሰዋስው ማስተማር ማለት ተግባቦታዊ ስነ ዘዴ ላይ ትኩረት የሚያደርግ አቀራረብ ነው። በዚህ ዘዴ አስቀድመን ለተማሪዎች የተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶችን በማስተዋወቅ የተግባቦት ፍላጎት እንድኖራቸው ማድረግ ነው። .............. 14

2.1.5.3. ሁኔታ ተኮር ሰዋስው ማስተማር (ንግግራዊ) አቀራረብ / SITUATION-BASED GRAMMAR TEACHING APPROACH/ .......... 15

2.1.5.3.1. ሁኔታ ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያት .......... 16

2.1.5.4. ውጤት ተኮር አቀራረብ (PRODUCT BASED APPROACH) .......... 16

2.1.5.4.1. ፅሁፍ ተኮር ማስተማር (TEXT BASED INSTRUCTION) .......... 17

2.1.5.4.2. ብቃት ተኮር ማስተማር (COMPTENCY BASED) .......... 17

2.1.5.5. ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ (CONSEICUNEES RASING APPROACH) .......... 18

2.1.5.6. ሂደት ተኮር (PROCESSES BASED APPROACH) .......... 19

2.2. መርሃ ትምህርት እና የቋንቋ የመማሪያ መጻህፍት .......... 20

2.2.1. የቋንቋ መርሃ ትምህርት ምንነት .......... 20

2.2.2. የመርሃ ትምህርት ፋይዳ .......... 21

2.2.3. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትና የመርሀ ትምህርት ግኑኝነት .......... 22

2.2.4.1. የመምህሩ መምሪያ ምንነት .......... 22

2.2.4.2. የመምህሩ መምሪያ ምን ምን ነገሮችን ሊያካትት ይገባል .......... 24

2.2.4.3. የመምህሩ መምሪያ ጠቀሜታ .......... 24

2.2.5. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት .......... 25

2.2.5.1. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ጠቀሜታ .......... 25

2.2.6. በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ (APPROACH) .......... 26

2.2.6.1. ግልጽነት .......... 26

ምዕራፍ ሦስት .......... 28

የአጠናን ዘዴ .......... 28

3.1. የጥናቱ ንድፍ .......... 28

3.2. የጥናቱ ተተኳሪዎች .......... 29

3.3. የናሙና አመራረጥ .......... 29

3.4. መረጃ መሰብሰቢያ ........................................................................................ 30

3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ..................................................................................... 30

ምዕራፍ አራት........................................................................................................ 32

4. ..................................................................................................የውጤት ትንተናና ማብሪ

4.1 የመማሪያ መጻህፍቱ፣ የመምህሩ መምሪያ እና የመርሀትምህርቶቹ አጠቃላይ ገጽታ ... 32

4.2. መማሪያ መጽሀፍቱ፣ በመምህሩ መምሪያ እና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ......................................................... 43

4.2.1. የሰዋስው ትምህርት ከግልጽነት አንጻር.......................................................... 43

4.2.2.የሰዋስው ትምህርት ከትክክለኝነት አንጻር ...................................................... 45

4.2.3. የሰዋስው ትምህርት ከተገቢነት አንጻር .......................................................... 47

4.2.4. የሰዋስው ትምህርት ከተመጣጣኝነት አንጻር .................................................... 49

4.3. መማሪያ መጻህፍቱ፣ በመምህሩመምሪያ እና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት............................................................................. 50

4.3.1.ተከታታይነት ........................................................................................... 50

4.3.2. ተለጣጣቂነት ......................................................................................... 60

4.3.3. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ............................................ 62

4.3.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት............................................................... 63

4.4. የውጤት ማብራሪያ ........................................................................................ 64

ምዕራፍ አምስት..................................................................................................... 67

ማጠቃለያ እና አስተያየት........................................................................................ 67

ዋቢ ጽሑፎች ........................................................................................................ 70

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሰዎች ቋንቋን ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ መናገር እና መልመድ ይችላሉ፤አንድ ሰው ቋንቋን ለመልመድ የሚያስችለውን ጤነኛ አእምሮ ይዞ እስከተፈጠረ ደረስ በአካባቢ የሚነገረው ቋንቋ ለመልመድ አይቸገርም፡፡ ነገር ግን ስለቋንቋ የተሻለ ዕውቀት ለማግኘትና የቋንቋውን ስርዓትና ሕግ ለማወቅ በትምህርት መታገዝ ይኖርበታል፡፡ ቋንቋን ማወቅ ማለት ሌሎች ሲናገሩ በማዳመጥ መልሶ መናገር ወይም መግባባት ሊሆን ይችላል፤ ስለቋንቋ ማወቅ ግን የቋንቋውን ውስጣዊ መዋቅርና ስርአት ጠንቅቆ ማወቅን ያካትታል፡፡

ጌታሁን (2004: IV) እንደሚያስረዱት የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ትክክለኛ የሆነውን ዓረፍተ-ነገር ትክክል ካልሆነው ለይቶ ሊነግረን ይችላል፡፡ ነገርግን ትክክለኛ ነው ያለውን ትክክል ለመሆኑም ሆነ ስህተት ነው ያለውን ስህተት የሆነበትን ምክንያት ሊነግረን አይችልም፡፡ይህንን ሊነግረን የሚችለው የቋንቋውን ስርዓት የሚያውቅ ባለሙያ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋን ማወቅና ስለቋንቋ ማወቅ የተለያዩ ናቸው፡፡ ስለቋንቋ ማወቅ የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅን የሚጠይቅ ሲሆን ለዚህ እውቀት የሚያበቃው ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ላይ የተመሰረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ተስፋዬ (1981:81) የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ሃሳቡን ለማስተላለፍ የሚጠቀምባቸው የቋንቋው የድምፅ አቀነጃጀት ስርዓት፣ የቃላት አደራደርና የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት አለው፡፡ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ተዋቃሪዎች ትርጉም የሚሰጥ መዋቅር ማስገኘት የሚችሉት የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መንገድ ሲቀናጁ ነው፡፡ በመሆኑም በቋንቋ መግባባትና ሃሳብን በተሟላ መልክ ለመግለጽ የቋንቋውን ስርዓት መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ እንደምንረዳው በአንድ ቋንቋ ለመገልገል ከቋንቋው ተጠቃሚ የሚጠበቀውን የቋንቋውን ስርዓት ሕግ ማወቅና በተግባቦት ጊዜም ጥቅም ላይ የሚያውለውን የሰዋስው ችሎታ ማዳበር እንደሚገባ ነው፡፡ እንዲሁም በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚነገሩ ቃላትን ብቻ ማወቅ በቂ ያለመሆኑ እና ይልቁንም ቃላቱ ተቀናጅተው ሰፊ መዋቅር የሚመሰርቱበትን መንገድ ተገንዝቦ መገልገል አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

በአንድ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ችሎታ ከሌለንና የቋንቋውን ሰዋስው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ካላወቅን በቋንቋ የምናደርገው የተግባቦት ሙከራ ደካማ ሊሆን እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ቋንቋን ስርኣታዊ የመግባቢያ መሣሪያ እንዲሆን ካስቻሉት ክስተቶች መካከል አንዱ ሰዋስው ነውና ስለዚህ የተሳካ ተግባቦት እንዲኖር ካስፈለገ የቋንቋውን ሰዋስው ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ Ur (2014: 74) እና Batstone (2012: 459-467) ያስረዳሉ፡፡

ባየ (2010: 10) ከአንድ የቋንቋ ተማሪ የሚጠበቀው ችሎታ ሁሉን አቀፋዊ የክህሎትና የስርዓት ቅንጅት መሆን እንዳለበት በመግለጽ የአንድ ቋንቋ አጠቃቀም ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን፤ ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የበለጠ እውቀት ያለው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎቱን ከስርዓቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ ስለሆነ ሰዋስውን መማርም ሆነ ማስተማር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ አንድን ቋንቋ በአግባቡ መገልገል ይቻል ዘንድ የሰዋስው እውቀት መኖር ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም በተለያየ ሁኔታ ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውልን የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓትን ጠብቆ በአግባቡ ለመገልገል የቋንቋውን ህግና ባህርያት ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በርካታ የሰዋስው አይነቶች ቢኖሩም ከተጠቃሚዎቹ እና ከዓላማው እንዲሁም ከአጠቃቀም አንጻር በዋናነት በሁለት ጎራ ይከፈላል፡፡ እነዚህም ለመማር-ማስተማር ዓላማ ተብሎ የተዘጋጀ ሰዋስው (Pedagogical Grammar) እና ለማጣቀሻነት Greenbaum (1996:25) (Reference ሰዋስው) ተብሎ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ምሁሩ ከጠቀሱት የሰዋሰው አይነት አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር በይበልጥ የሚቀራረበው ለመማር-ማስተማር አላማ የተዘጋጀው የተማሪዎቹን የእውቀት ደረጃ፣ ችሎታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ ሰዋስዋዊ ይዘት ያለው የተማሪው መጽሀፍ ነው፡፡ ይህ የሰዋስው አይነት ተማሪዎች በትምህርት ቤት በመምህራን እገዛ እንዲጠቀሙ ተብሎ የሚዘጋጅ መጽሀፍ ነው፡፡

የሰዋስው ትምህርት በተደራጀ መልክ በዋነኝነት ከሚሰጥባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የተማሪው መጽሀፍ ሲሆን የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በቋንቋ መርሀ ትምህርት የተካተተውን ይዘት መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁና ተማሪው የሚጠበቅበትን የባህሪ ለውጥ

እንዲያመጣ የሚያግዙ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም አንድ የክፍል ደረጃን መሠረት በማድረግና መርሃ-ትምህርትን መነሻ በማድረግ የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ Jeongae, Hyeseung እና Cheryl (2019:3) ፡፡

መርሀ-ትምህርት ተግባራዊ ሲሆን የሚችል መማር ማስተማር ክንውን ማሳያ ሲሆን ተግባራዊነቱም የሚተረጎመው በመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ በመርሀ-ትምህርቱ፣ በመማሪያ መጻህፍቱና በመምህሩ መምሪያ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ለትምህርት ውጤት መሳካት የላቀ ሚና አለው፡፡

Bridge (2018: 23) የመምህሩ መምሪያ መምህሩ ምን ማስተማር እንዳለበት እና እንዴት ማስተማር እንዳለበት ዝርዝር አሰራር በመጠቆም የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲቀላጠፍ ከማድረግ ባሻገር በመርሀ-ትምህርቱና በመማሪያ መጽሀፉ መካከል ድልድይ በመሆን ያገለግላል፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ለመምህሩ ጽንሰ ሀሳብን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እያዋሀደ የሚያስተምርበትን አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

ይህን ሃሳብ McDonough & Shaw (1993: 13) ሲያጠናክሩት መርሃ-ትምህርት አጠቃላይ የመማር ማስተማር ጉዳዮችን የያዘ፣እንዴት መማርና ማስተማር እንደሚቻል የሚያመላክት ሲሆን መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ደግሞ በመርሀ-ትምህርቱ ላይ የሰፈሩትን አላማና ይዘት ለመተርጎም በሚያስችል ሁኔታ የሚሰናዱ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የመማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ መርሀ-ትምህርቱን መሰረት በማድረግ መርሀ-ትምህርቱ ላይ የሰፈረውን አላማና ይዘት ከግብ ለማድረስ የሚዘጋጁ ሲሆን ተገዢነታቸውም ለመርሀ ትምህርቱ ነው፤ ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉና የመምህሩ መምሪያ ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቱ ይመነጫሉ ማለት ይቻላል፡፡

Stern (1992) የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ የሰዋስው ይዘቶችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይቻል ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ስነ-ልሳናዊ ፣ ስነ-ትምህርታዊ እና ስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሀሳቦች መሰረት አድርገው ሲዘጋጁ መርሀ-ትምህርቱን መነሻ ማድረግ እንዳለባቸው ይመከራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዝግጅት ወቅትም ይሁን በሰራ ላይ ከዋሉም በኋላ ተከታታይ ግምገማ ወይም ፍተሻ ሊደረግባቸው እና ከዚያም በሚገኙ ምላሾች መሰረት ሊሻሻሉ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሀ-ትምህርቱ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸውና ለተማሪዎች ቋንቋ መዳበርም አስፈላጊነታቸው የጎላ መሆኑን እንዲሁም በሚዘጋጁበትም ወቅት ለክፍል ደረጃው በሚገባ ተደራጅተውና ተመጥነው መቅረብ እንዳለባቸው ነው፡፡

ይህ ጥናት ትኩረት የያደረገው በ2014 ዓ.ም በታተሙት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት አቀራረብ ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በ2014 በታተሙት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሀትምህርቶች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ያላቸውን ተጣጥሞሽ ለመፈተሽ አጥኚውን ያነሳሳው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. አጥኚውን ለዚህ ጥናት ያነሳሳው ዋነኛ ምክንያት በ7ኛ ክፍል ተመድባ በምታስተምርበት ወቅት አንዳንድ ተማሪዎች የመሠላቸት እና የመደናገር እንዲሁም ለትምህርቱ ፍላጎት የማጣት ነገር የሚታይባቸው በተተኳሪዎቹ መፅሃፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አላማ፣ትዕዛዝ፣ምሳሌ እና ማብራሪያዎች ግልጽ አለመሆን ይሆን? አቀራረቡ ሳቢ አለመሆን ይሆን? ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት በመማሪያ መጻህፍቱ፣በመምህሩ መምሪያና በመርሀ-ትምህርቶች የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ ለመፈተሽ ካለው ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡

ለ. አጥኚው በዚህ ጥናት ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ለመመልከት ሞክሯል፡፡ ከነዚህም ጥናቶች ውስጥ ሰሚራ (2010) «በደቡብ ክልል በ2013ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ» በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የጥናቱም ውጤት እንደሚያሳየው በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በጠቅላላ በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን ከጥናቱ ይህ ውጤት መገኘቱ ይህን ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በሌላ መልኩ ባዩ (2004) « በደቡብ ክልል በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አቀራረብ አደረጃጀት ግምገማ» በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ እንደሚያሳየው በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች የተወሰኑት መርሀ-ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ መርሀ-ትምህርቱን መሰረት

ያላደረጉ መሆናቸውና የግልጽነት ችግር ያለባቸው መሆኑን ከጥናቱ ግኝት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ጥናቶች ውጤት በመነሳት በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጽሃፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ለደረጃው ከተዘጋጁት መርሀ-ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ ለማረጋገጥ ፍላጎት ያደረበት በመሆኑ፤

ሐ. አጥኚው ለድህረምረቃ ማሚያነት ከወሰዳቸው የስነ-ልሳን ኮርሶች ውስጥ ስነ-ትምህርታዊ ሰዋሰውን በሚመለከት ካገኘው ግንዛቤ በመነሳት በመማሪያ መጽሐፉቱና በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎችን የተከተሉ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ ፍላጎት ያደረበት መሆኑ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ለ7ኛ እና ለየ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀ ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ ዋና አላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት፡

ሀ. በተተኳሪዎቹ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን መፈተሽ፡፡

ለ. በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ለክፍል ደረጃው በተዘጋጁት መርሃ-ትምህርቶች ላይ መመስረት አለመመስረታቸውን መፈተሽ፡፡

ሐ. በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች አኳያ እንዴት እንደቀረቡ መፈተሽ፡፡

መ. በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመማሪያ መጽሃፍት አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር እንዴት እንደተደራጁ መፈተሽ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ሀ. ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣የመምህሩ መምሪያ እና መርሀ-ምህርት ለሚያዘጋጁ ማሻሻያ በሚያደርጉበት ጊዜ እንደግብዓት በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

ለ. በሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ረገድ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጽሃፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ ፈትሾ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በማሳየት፤ የሚመለከታቸው አካላት በቀጣይ ለሚደረጉት ጥናት የበኩሉን አስተዋጾ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል፡፡

ሐ. ወደፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት ተጨማሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሠን

ይህ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱ በ2014 ዓ.ም በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አማካኝነት በታተሙት የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሃፍቱ፣ በመምህሩ መምሪያና በመርሀ-ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች፣ ክሂሎች እና ስነ ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችና ሌሎች ጉዳዮች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡ ከተተኳሪዎቹ እርከን በታችም ሆነ በላይ ያሉትን መማሪያ መጽሃፍትም ሆነ አስቀድመው በስራ ላይ ውለው የነበሩትን መማሪያ መጻሕፍትና መርሀ-ትምህርቶች የሚመለከት አይሆንም፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱ በ2014 ዓ.ም በሲዳማ ብሄራዊ ክልል አማካኝነት በታተሙት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት፣ አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ብቻ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

ይህ ምዕራፍ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተዛማጅ ድርሳናት የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሰዋስው፣መርሀትምህርት፣የመምህሩ መምሪያና መማሪያ መጻሀፍትን የሚመለከቱ ትወራዊ ስራዎችና ቀደምት ጥናቶች በስፋት ተዳሰው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል የሰዋስው ምንነት፣የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አጭር ታሪክ ፣ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት፣ የሰዋስው ትምህርት ይዘት፣የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች፣የመርሀትምህርት ምንነት፣ የመርሀትምህርት ጠቀሜታ፣የመምህሩ መምሪያ ምንነት፣ጠቀሜታ፣የመምህሩ መምሪያ ጠቀሜታ፣የመማሪያ መጻሀፍት ምንነት፣የመማሪያ መጻሀፍት ጠቀሜታ፣ በመማሪያ መጸሀፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመማሪያ መጻሀፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀት እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ተዳሰዋል፡፡

## 2.1. የቋንቋ ሰዋስው

### 2.1.1. የሰዋስው ምንነት

‹ሰዋስው› የሚለው ቃል በብዙ ሰዎች በተለያየ መንገድ ይገለጻል፡፡ በርካታ ምሁራን የሰዋስውን ምንነትን አስመልክተው የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል በተለያዩ ጊዜያት ስለሰዋስው ምንነት ከተሰነዘሩት ብያኔዎች ለአብነት የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡ Larsen-Freeman (2001: 51)፡፡ ሰዋስው የአንድ ቋንቋ ሕግ ነው፡፡ ሰዋስው በትክክለኛው ተግባራዊ ገደቦች የሚተዳደሩ ትርጉም ያላቸው መዋቅሮች እና ቅንጣቶች ስርዓት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሰዋስው የተለያዩ ቃላትን፣ ሀረጋትን እንዲሁም አረፍተ ነገሮችን ለመቅረጽ የሚስያስችሉ ሕጎች መግለጫ ነው፡፡

Brown (2000: 362) «ሰዋስው ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ በስርዓት ተቀናጅተው የሚፈጥሩትን መዋቅርና እርስበርሰስ ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት የቋንቋ ስርዓትና ህግ ነው» በማለት ይገልፃሉ፡፡ Hdfield & Hdfield (2008: 18) «ሰዋስው ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን አደራደር፣ አወቃቀርና አደረጃጀት እንዲሁም ቅርፃቸውን በመለወጥ እንዴት ትርጉም ሊያስገኙ እንደምችሉ የሚገልፅ የቋንቋ ስርዓት ነው»፡፡

ከሙህራኑ ገለጻ እንደምንረዳ ሰዋስው የቋንቋ አጠቃቀምን የተሳካ የሚያደርግ፣ ቋንቋ የሚገዛበት ህግ እና ስርዓት ነው፡፡ ይህም ስርዓት ከድምፅ አንስቶ ደረጃ በደረጃ እየሰፋ እስከ አረፍተ ነገር ያለውን አጠቃሎ የሚመለከት ሲሆን ቃላት ተቀናጅተው ትክክለኛ አረፍተ ነገር ለመመስረት የሚቀናጁበትና ትርጉም የሚሰጡበትን የቋንቋ ስርዓት እንደሆነ የሚመለከት ነው፡፡

Nelson (2001: 4) ስለ ሰዋስው ምንነት ሶስት የተለያዩ ትርጓሜዎችን አስቀምጧል፡፡

1. ሰዋስው ትክክለኛ ትርጉም ለማስተላለፍ የተደረደሩ የቋንቋው መደበኛ ቃላት ስብስብ ነው፡፡
2. ሰዋስው መደበኛ የቋንቋ ትንተና እና የቃላት አደራደርን የሚመለከት የቋንቋ ሳይንስ ነው፡፡
3. ሰዋስው የሚለውን ቃል እራሱ "የቋንቋ ሥነ ምግባር" ነው፡፡ በማለት ስለሰዋስው ምንነት ገልጻል፡፡

Greenbaum (1982) የቋንቋውን አጠቃቀም እና በቋንቋው የመረዳት ችሎታ እንዲሁም የቋንቋውን ህጎችና ደንቦች ማወቅን፤ እንዲሁም የአረፍተ-ነገሮችን ሰዋሰዋዊ አወቃቀር በመረዳት በቦታውና በጊዜ በብቃት የመግባባት ችሎታን የሚያጠቃልል ነው፡፡እንዲሁም Chomesky (1978) "ሰዋስው በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚፈለገውን የግንኙነት ተጽዕኖ ለማሳካትና ሰዎች ከሰዎች የተቀበሉትን ዕውቀት በብቃት ለመጠቀም የሚያስችል ችሎታ ነው ማለት ይቻላል፡፡"

Donald & Kneale (2001: 79) እና Williams (2005: 41) ይህንን ሀሳብ ሰዋስው በማንኛውም ተግባቦታዊ ክንውን መልዕክትን በብቃትና በስኬት ለማስተላለፍ የሚረዳ ሰፊ የሆነ ፅንሰ ሃሳብ ያለው የቋንቋ ክፍል ነው፡፡ ይህም ድምጾች እንዴት ተቀናጅተው ቃላት እንደሚመሰርቱ ቃላትም እንዴት ተቀናጅተው ሀረግና ዐረፍተነገር እንደሚመሰርቱና ቃላት በተዋቀሩበት በዚያው አውድ ውስጥ እንዴት ፍቺን እንደሚያስገኙ የሚያሳይ ጽንሰሀሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ ሙሁራን እንደተገለፀው ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርዓትና የአጠቃቀም ህግ የሚመለከት ነው፡፡ የቋንቋ ስርዓትና ህግ ሲባል ሁሉም ቋንቋዎች የራሳቸው የሆነ የተለየ ስርዓትና የሚገዙበትን ህግ የሚያካትት ነው፡፡ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ሃሳቡን በፅሁፍ ወይም በንግግር ለማስተላለፍ የሚጠቀምባቸውን የድምፅ ስርዓት፣ የቃላት አደራደር፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀርና አመሰራረት ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም

በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ተዋቃሪዎች ትርጉም የሚሰጥ መዋቅር ማስገኘት የሚችሉት የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መንገድ ሲቀናጁና ሲደራጁ ብቻ ነው፡፡

## 2.1.3. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት

ሰዋስው የቋንቋ አወቃቀሮችንና በቋንቋ አማካይነት የሚተላለፉ መልእክቶችን በተመለከተ ትክክለኛ ግንዛቤ ለተማሪዎች የሚያስጨብጥ በመሆኑ ቋንቋን በትክክል የመጠቀም ችሎታና ብቃታቸው እንዲጨምር እንዲሁም በዐውደ-ጽሁፈት ውስጥ የአረፍተ-ነገር መዋቅሮች እንዴት እንዲመሠርቱ ለተማሪዎች በማመልከት ይረዳል፡፡ ሰዋስው ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ከትንሹ የቋንቋ መሰረት ከሆነው ድምጽ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ እስከ ከፍተኛው የዓረፈተ ነገር አቀነጃጀት ያለውን ስርዓት እንዲያውቁ ይጠቅማል፡፡

የሰዋስውን ትምህርት ለምን መማር አንዳለብን Krahnke (1985: 598) & Terrell(1991: 54) ሲያስረዱ ለተማሪዎች የተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም ሰዋስው ወሳኝ ሚናን ይጫወታል የሰዋስው ችሎታ ለተማሪዎች ቃላትን እና መልዕክቶችን ትርጉም ባለው መልክ እንዲያደራጁ፤ በንግግር እና በፅሁፍ ዝግጅቶች የተሳኩ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲገነቡ ያስችላቸዋል፡፡ የሰዋስው መኖር ተማሪዎች ዓረፍተ ነገሮችን ለመረዳት በቂ እውቀት ኖሯቸው ትርጉም ያለውን መልዕክት እንዲያስተላልፉ ይረዳቸዋል፡፡ ሰዋሰውን በትክክል አለመጠቀም ደግሞ የተዛባ መልዕክት እንዲተላለፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የባለቤት እና ግሶችን አለመጣጣም፣ የተሳቢ አመልካች መገደፍ፣ የቁጥር አለመስማማት ወዘተ የመሳሰሉት ስህተቶች ስለሚፈጠሩ ተግባቦቱ የተሳካ አይሆንም፡፡

Tabbert (1984: 39) ሰዎች ከሰዎች ጋር ውጤታማ ግንኙነትን እንዲመሠርቱ የሰዋስው ችሎታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ያለ ሰዋስው ተግባቦት ትርጉም አልባ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሰዋስው በወጉ የተስተካከለ ንባብ እና የጽሑፍ ሥራዎችን እንድናቀርብ ያስችለናል ፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ሰዋስው ስለ አንድ ጉዳይ በቦታውና በጊዜው በወጉ የተሰካኩ ቃላትና አረፍተ ነገሮችን ለማፍለቅ የሚያስችለንን ብቃት እና ችሎታ ይሰጠናል፡፡

Tabbert (1984: 40) "ሰዋስው ለተማሪዎች ቃላትና ዓረፍተ-ነገሮችን እንዴት እንደሚያዋህዱና የተስተካከሉ ዓረፍተ-ነገሮችን እንዴት እንደሚፈጥሩ የሰዋሰው ዕውቀት ይሰጣቸዋል፡፡" እንዲሁም ትልቁን ክፍል ስለሚገነቡት ዓረፍተ-ነገሮች ቅርፅ እና ተግባር በተሻለ ሁኔታ እንድንገነዘቡ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

Lindblom (1978: 1) የሰዋስው ትምህርት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው ። የሰዋስው ችሎታ ለቋንቋ ብቃት የቋንቋ አወቃቀር እና ታሪክ ጥናት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ልብ ሊባል ይገባል። ትክክለኛ የሰዋስው ትምህርት አሰጣጥ ተማሪዎች ቋንቋውን በትክክል እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ይመራቸዋል። Azar (2007: 8) ሰዋስው የማስተማርን አስፈላጊነት ሲገልጽ ሰዋስውን ማስተማር አስፈላጊ ከሆነባቸው ጉዳዮች አንዱ ለተማሪዎች የቋንቋ ምንነት እንዲገነዘቡ መርዳቱ ነው፣ ማለትም ቋንቋን የምንናገረው፣ የምናነበው፣ የምንሰማው እና የምንጽፈው የቋንቋን ምንነት ስንገነዘብ ነው። ያለ ሰዋስው ትርጉም ያለው መልዕክት ማስተላለፍ አስቸጋሪ ነውና Ellis (2006: 84) እንደሚሉት «ትክክለኛ አረፍተ ነገሮችን ለመገንባት የሰዋሰው እውቀት አስፈላጊ ነውና።»

ከሙሁራኑ ገለጻ እንደምንረዳው አንድ ሰው ሰዋስውን በአግባቡ መጠቀም ከቻለ በሰዓቱ እና በቦታው የተፃፉና ተላለፉ መልእክቶችን በሚገባ መረዳት ይችላል። ትክክለኛ ሰዋስው ከተሳሳተ ግንዛቤ የሚጠበቅ ከመሆኑም በላይ ሀሳባችንን በብቃትና በአግባቡ እንድንገልፅ ይረዳናል። የምንግባባበት መንገድ በሙያችን እና በማህበረሰባችን ውስጥ ትልቅ ቦታ ይኖረዋል። ሰዋስው ለቋንቋው ተጠቃሚዎች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ሀሳቸውን በአግባቡ የመግለፅ እና የመግባባት አቅማቸውንም ያጎለብታል ።

አንድን ቋንቋ የሚናገር ሰው የዚያ ቋንቋ ሰዋስው አውቆም ይሁን ሳያውቅ ሊጠቀም ይችላል፤ ነገርግን ቋንቋውን አውቆ መጠቀምና ሳያውቁ መጠቀም የተለያዩ ናቸው። Kohli (1984: 116)ይህንን ሀሳብ ሲያብራሩ ሁለት የመኪና ሾፌሮችን አሰቡ። የመጀመሪያው አሽከርካሪ መንዳት ብቻ ያውቃል እንጂ ስለመኪናው የውስጥ ክፍሎች ምንም አያውቅም። በመኪናው ላይ አንዳንድ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ ረዳት እንደሌለው ይሰማዋል። ሁለተኛው አሽከርካሪ መንዳትም የመካኒክስነቱን ስራ አብሮ ይችላል። ስለዚህ መኪናው መንገድ ላይ ቢበላሽ ስጋት አይገባውም። ሰዋስው የሚያውቅ ሰውም እንደዚህ ሁለተኛው ሾፌር ነው። ሰዋሰውን ማወቅ በግልፅ፣ ትርጉም ባለው መልኩ እና ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመግባባት ይረዳል። የሰዋስው እውቀት ያለው ሰው ነገሮችን በቀላሉ እና በግልጽ ማስረዳትና መረዳት ይችላል። ስለዚህ ቋንቋን ማወቅ ብቻ ሳይሆን አጠቃቀሙንና አወቃቀሩን ጭምር ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ሰዋስውን መማር አስፈላጊ ነው።

Ur (1999) ሰዋስው ድምጾች፣ቃላት፣ሐረጋት እና አረፍተነገሮች እንዴት አንድ ላይ እንደሚጣመሩ ለማወቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ የምንችልበትን መንገድ የሚያሳይ ነው። በሌላ አገላለጽ ሰዋስውን ማስተማር የቋንቋውን አወቃቀር፣ ትርጉሙን እና አጠቃቀሙን ማስተማር ማለት ነው።

Richards & Renandya (2002: 145-146)፡፡ ሰዋስው ለማስተማር ሁለት ጥሩ ምክንያቶችን እንዳሉ ይጠቁማሉ፡፡

ሀ) **ግንዛቤ-** ሰዋስው አረፍተነገር መዋቅሮችን እንዴት እንደሚገነቡ እና እንደሚጠቀሙ ለማወቅና የተለመዱ የትርጉም ዓይነቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማስተላለፍ ያስችላሉ፡፡ ያለ እነዚህ አወቃቀሮች የተሳኩ ዓረፍተ-ነገሮችን መመስረትም መረዳትም ከባድ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህን አወቃቀሮች ለማወቅና አውቆም ለመጠቀም ሰዋስውን መማር አስፈላጊ ነው፡፡

ለ) **ተቀባይነት-** በአንዳንድ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች በአድማጮች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው እንዲሆኑ ሰዋስውን መማር አስፈላጊ ነው፡፡ ያለሰዋስው ዕውቀት የሚነገር ንግግር ወይም የሚተላለፍ መልዕክት ብዙም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም ለተማሪዎች የቋንቋ ምንነትን እንዲገነዘቡ እንዲሁም ነገሮችን በቀላሉ እንዲረዱና ሐሳባቸውን ተቀባይነት ባለው መንገድ እንዲያስተላልፉ እና ፅንሰ ሀሳቦችን በመጠቀም የጊዜ ግንኙነቶችን ለመግለጽ፤ የስሞችን፣ የቅጽሎች ግሶችን፣ የአንቀጾች እና የሀረጎችን ቅንጅት በአግባቡ ለመግለጽ ይረዳል፡፡ Azar (2007: 1-5) ሰዋስው የቃላትን አገባብ፣ ከድምጽ አንስቶ እስከ አረፍተነገር ያሉትን ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች እንዲሁም እንደ ስም ወይም ግስ ያሉ ቁልፍ ቃላትን ያለ ፍቺ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡ የቋንቋ ሰዋስው ችሎታ የቋንቋውን የቃል ክፍሎች ግንኙነት እንዲያውቁና ሰዋስዋዊ ፅንሰ-ሀሳቦችን በተሻለ መንገድ ተረድተው እንዲጠቀሙ ያስችላል፡፡

Browen (1994) የቋንቋ ትምህርት የተማሪውን ክህሎት ከማዳበር ባሻገር ተማሪው ሊገነዘበው የሚገነባውን የሰዋስው ዕውቀት ጭምር ማካተት ይኖርበታል፡፡ ይህም ቋንቋውን በማስተማር ወቅት ከተግባቦት በተጨማሪ የአጠቃቀም ስርቱን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የቋንቋ እውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎትን ከነስርአቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡

Mulroy (2003: 118) ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩት ሰዋስው ሰዎች በሁሉም ቦታ የተሳካ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የተሳካ ተግባቦት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ የቋንቋን ግንዛቤ ያሰፋል፡፡ ምክንያቱም በግልጽ የተቀመጡ ሕጎች ተማሪዎች በአረፍተ-ነገሮች ውስጥ ህጎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋልና፡፡

ቋንቋ በህግ የሚገዛ ነው፤ ህጉም ደግሞ ሰዋስው ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋን ከሰዋስው ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ድምፆችና ምዕላዶች ስርዓት ይዘው ካልተዋቀሩ በስተቀር ትርጉም አዘል ቃላትን አይመሰርቱም፡፡ ቃላትም በስርዓት ካልተዋቀሩ በተለያየ አውዱ

ውስጥ የሚኖራቸውን ፍቺ ያጣሉ፡፡ ስለዚህም ትክክለኛውን የአወቃቀር ስርዓት ተጠቅሞ ያለ እንቅፋት በቋንቋው ለመግባባት ህጉን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የሰዋሰው ትምህርት አብይ አላማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋስው የቋንቋ አወቃቀሮችንና በቋንቋ አማካይነት የሚተላለፉ መልእክቶችን በተመለከተ ትክክለኛ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ በመሆኑ የተማሪዎችን ቋንቋን በትክክል የመጠቀም ችሎታና ብቃት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

## 2.1.4. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

ሰዋስውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በሌሎች የቋንቋ ክፍሎች በክሂሎችና በስነጽሁፍ የትምህርት ይዘቶች ውስጥ ተካተው እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም Batstone (2012: 460) «ቋንቋ ያለ ሰዋስው ጎደሎ ነው፤ የተሟላ አይደለም፡፡» በበርካታ የቋንቋ አሃዶች ውስጥ ሰዋስው የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ ሰፋ ያለ የቋንቋ ክፍሎችን ያካልላል፡፡ ሰዋስው የቋንቋ መሰረት ከሆነው ድምፅ አንስቶ እስከ ሰፊው የቋንቋ አካል ያለውን ስርዓት የሚመለከት መሆኑ ለይዘት ሽፋኑ ስፋት ማሳያ ነው፡፡ Livia (2006: 8) «የሰዋስው ትምህርት የአንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምፅ አሰካኩ እስከ ዓረፍተነገር አመሰራረቱ ድረስ ያለውን ሂደት የሚያሳይ ነው፡፡ ይዘቱ የስርዓት ነው» በማለት የይዘቱን ሰፊነት ይገልፃሉ Stern (1992: 127) ሰዋስው የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በጣም ሰፊና ይዘቱም ስነ ድምጽ፣ ስነ ምዕላድ፣ ስነ አገባብ፣ ስነ ፍቺ እና የዲስኩር ትንተና የሚያካትት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ጌታሁን (2014: iV) «ሰዋስው በቋንቋ ጥናት ውስጥ ስርዓትን የሚመለከት ክፍል ነው» በማለት እንደጠቀሱት የአንድን ቋንቋ ድምፅ አፈጣጠር፣ አይነትና ባህርይ የቃላት እርባታ፣ ምስረታና አደራደር ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች የመሳሰሉት የሚዋቀሩበትን ስርዓት የሚመለከቱ ይዘቶች በሰዋስው ትምህርት ይዘት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

Batstone (2012: 464) ሰዋስው በቋንቋ ውስጥ ሰፊውን ክፍል የሚይዝ በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ለማስተማሪያነት የሚቀርቡት የሰዋስው ይዘቶች እንደየደረጃው አስፈላጊነታቸው ታይቶ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ለማስተማሪያነት በመርሃ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ይዘቶች እንደየክፍል ደረጃው ትምህርቱ ለሚሰጣቸው ተማሪዎች ምን ያህል አስፈላጊ ናቸው? ምን ጥቅም አላቸው? የሚሉትን ጉዳዮች ከግምት በማስገባት ሊካተቱ ይገባል፡፡ እንደሁም የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ሊያሳኩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

ሰዋስው በጣም ሰፊና በውስጡ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎችን አካቶ የሚይዝ የእውቀት ዘርፍ ነው። ስለሰዋስው ይዘት ፈርጀ ሰፊነት Ur (1996: 87-88) ሲገልጹ ከትንሹ የቋንቋ አሀድ አንስቶ እስከ አረፍተ ነገር ያለውን መዋቅር የሚመለከት ጥናት መሆኑን ይገልጻሉ። በዚህ መሰረት ሰዋስው ከድምፅ ጀምሮ እየሰፋ እስከ አረፍተ ነገር ያሉ መዋቅሮችን (ስነ ድምፅ፣ ስነ ምዕላድ፣ ስነ አገባብ፣ ስነ ፍቺ እና የመሳሰሉት) አካቶ የሚይዝ ጥናት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

እንደሌሎች የትምህርት ይዘቶች ሁሉ ለመማር ማስተማር ዓላማ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተቀርጸው ከሚቀርቡባቸው ሰነዶች ውስጥ የቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጻህፍት ሲሆኑ በነዚህ ሰነዶች ውስጥ ከስነድምጽ አንስቶ እስከ ስነፍቺ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች እንደተሰጣቸው ቦታና ትኩረት ተካተው ይገኛሉ።

## 2.1.5. የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች

የሰዋስው ትምህርት አላማን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የአቀራረብ መርሆዎችን በመንደፍ ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። በተለያዩ መሁራን ከተገለጹ አቀራረቦች መካከል በዘመናዊ ሰዋስው አቀራረብ ስር የተካተቱትን ለማንሳት እሞክራለሁ።

### 2.1.5.1. ተግባቦታዊ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ COMMUNICATIVE GRAMMAR TEACHING APROACH (CGTA)

Richards (2006: 10-20) ተግባበታዊ ሰዋሰው ማስተማር አቀራረብ ከ1970ዎቹ እስከ1990ዎቹ የነበረ ሲሆን ጥንታዊ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ዘመናዊ የሆነበትና ከ1990ዎቹ ጀምሮ በሰፊው ተግባራዊ የተደረገ የሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ነው። ይህ አቀራረብ ተግባራዊ ሲደረግ ትኩረት የሚሰጥባቸው ነገሮች ተማሪዎቹ የሚማሩበት አውድ፣የተማሪዎች እድሜ፣ የትምህርት ደረጃቸውን የመሳሰሉት ይገኙበታል። የተግባቦታዊ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ዋና ግቡ ተማሪዎችን የተለያዩ ማህበራዊ አውድ በማዘጋጀት በቋንቋው እንዲግባቡ ማለማመድ ነው። በዚህ አቀራረብ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ ለመጉላት ያገለግላል። ዋና ትኩረቱ ቋንቋን በተጨባጭ አውድ ውስጥ ተማሪዎች መጠቃማቸውን አፅዕኖት ይሰጣል እንጂ በትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ አይደለም በተግበቦታዊ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ የመምህሩ ስራ ስለ ሰዋስው ዝርዝር ገለፃ መስጠት ብቻ ይሆናል። የዚህ አቀራረብ ትኩረቱ የሰዋስው ህግ ዕውቀት ስላልሆነ ተማሪዎች ተግባሩን በሚያከናወኑበት ጊዜ ስህተት ሊሠሩ ይቻላሉ፤ በዚህ ስህተት ላይ

መምህሩ ምንም ዓይነት ማስተካኪያ አያደርግም ስለዚህ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት ከተሰጠው ተግባርና አውድ በመነሳት የቋንቋ አጠቃቀምን ይማራሉ፡፡

## 2.1.5.2. ተግባር ተኮር አቀራረብ/TASK BASED APPROCH/

Richards & Rodgers (2001: 151) ስለተግባር ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ሲገልጹ ተግባር ተኮር ሰዋስው ማስተማር ማለት ተግባቦታዊ ስነ ዘዴ ላይ ትኩረት የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ አስቀድመን ለተማሪዎች የተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶችን በማስተዋወቅ የተግባቦት ፍላጎት እንድኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

Nunan (1998: 2) «ስለተግባር ተኮር አቀራረብ ሲገልጽ ተግባር ማለት በውጭ የምንመለከተውን ነገር ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት ማስተማር ማለት ነው፡፡» ይህም በሚሆንበት ጊዜ ተግባር ወደ ማስተማር ባህርይ ተሸጋገረ ማለት ነው፡፡

ተግባር ተኮር ማስተማር አቀራረብ ማለት ቋንቋን በመረዳት የአንድን ተግባር እንቅስቃሴ በሂደት ወደ ውጤት ማድርስ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ በድምጽ የተቀዳ ቅጂ በማዳመጥ አንድን ተግባር እንዲያከውኑ በማድረግ ስለዚያ ነገር አሰራር በቋንቋ አማካይነት እንዲረዱ ማድረግ ማለት ነው ይህም ትግባር ቋንቋን በመጠቀም የሚከናወን ይሆናል፡፡ሌላው ተግባርን አስቀደመን ዓለማ ማድረግ አለብን፡፡ ለምሳሌ ግድግዳ ቀለም የሚቀባው አንድ ሰው ቢጠየቅ የሚመልሰው መልስና በተመሳሳይ ደብዳቤ ሚፅፍን ሰው ለምን እንደሚፅፍ ቢጠይቅ የሚሰጠው ምላሽ አንድ አይደለም፡፡ ቀለም የሚቀባው ለገንዘብ፤ ለማሳመር፣ ሊለን ይችላል፡፡ ደብዳቤ የሚፅፈው ትክክለኛ የደብዳቤ አፃፃፍ ለመለማመድ፤ ሊል ይችላል፡ በዚህ መሠረት ትክክለኛውን የቋንቋ ሰዋሰው በተግባር ሊረዳው ይችላል፡፡ስለዚህ ተግባር ቋንቋን በመፍጠር ልምምዱ ይካሄዳል፡፡ ተግባር ተከር ሰዋስው አቀራረብ ማለት በክፍል ውስጥ የሚከናውን ስራ ማለት ነው፡፡ ይህን ተከትለው ተማሪዎች በራሳቸው ጥበብ ትርጉም ያፈልቃሉ ወይም ከተላሚው ቋንቋ ሰዋስው ጋር በማገናኘት ትርጉሙን ይገልፃሉ፡በዚህ ወቅት የተማሪዎች እይታ ከቅርፅ ይልቅ ትርጉም ማፈለቅ ይሆናል በዚህ ሂደት በተግባሩ፣ መጀመሪያ መካከል እና መጨረሻ ድረስ ተግባቦት ይፈፅማል ማለት ነው፡፡

Richards (1986: 56) ስለተግባር ተኮረ ማስተማር ዘዴ እንደገለፅው ተግባር ተኮር ማስተማር ዘዴ ፣ የተፈላገውን ውጤት ለማስመዝገብ ምን ምን ነገሮች መማሏት እንደለባቸው መ/ሩ በዝርዝር ለይቶ ማወቅ፤ ከዚያ በኋላ ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ዓይነት ተግባራት በቋንቋ ማስተማር ውስጥ በመጠቀም የቋንቋ ማስተማር የበለጠ ተግባበታዊ እንዲሆን በክፍል ውስጥ መተግበር አንዱ ቋንቋን ለቋንቋ ዓለማ መጠቀም ነው፡፡ ተግባሩ ግን መግባባት ነው፡፡

Thornbury (1999: 129) ስለተግባር ተኮር ሰዋሰው ማስተማር አቀራረብ ሲገልጽ "ተማሪው የሚማረውን ተግባር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በመያዝ ትክክለኛነቱን ማስጠበቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በየጊዜው የሚማሩትን ሰዋስው ከትርጉም ጋር አያይዘው ያስቀምጣሉ ማለት ነው፡፡"

በአጠቃላይ Nunan (1998), Ellis (2006), Richards & Rodgers (2001) & Thornbury (1999) እንደገለጹት ተግባር ተከር አቀራረብ ተግባር ማለት የሥራ ዕቅድ ማለት ሲሆን ተማሪዎች ቋንቋን በትክክለኛ መንገድ በመጠቀም የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት የሚያደርጉት ሂደት ውጤት እና ውጤቱም ከተሰጠው ይዘት አንፃር ትክክል ነው ተብሎ ሊለካ የሚገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተግባሩም ደግሞ አስቀድመው ለትርጉም ትኩረት እዲሰጡ እና የራሳቸውን ቋንቋ እንደምንጭ እንዲጠቀሙ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል ፡፡

## 2.1.5.3. ሁኔታ ተኮር ሰዋስው ማስተማር (ንግግራዊ) አቀራረብ / SITUATION-BASED GRAMMAR TEACHING APPROACH/

Richards & Rodgers (1986: 34) ስለ ሁኔታ ተኮር ቋንቋ ሰዋሰው አቀራረብ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ ሁኔታ ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ በ1920ዎቹ እና 1930ዎቹ አከባቢ የተጀመረ ሲሆን ለዚህ አቀራረብ መጀመር ምክንያቱ ደግሞ ብሪታንያዊያን ተግባራዊ ስነ- ልሳን ማስተማር መጀመራቸው እንደሆነ ይገለጻል፡፡

ይህ አቀራረብ በ1990ዎች አካባቢ በጥቂት የቋንቋ መምህራን ዘንድ እየተወደደ የመጣና እስከአሁንም ድረስ በተግባር ላይ ያለ አቀራረብ ነው፡፡ ይህን አቀራረብ በአውስተራሊያ በሰፊው በስራላይ የዋለ አቀራረብ ነበር ፡፡ አውስተራላውያን ይህን አቀራረብ እንዲጠቀሙ ያስገደዳቸው ዋናው ጉዳይ ሀገር በስደት ወደ ሌላ ሀገር በሚሄዱበት ወቅት እንግሊዘኛን ለመጠቀም እንድያስችላቸው መጠቀም ሲጀምሩ በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቀና በሰፊው መጠቀም የተጀመረ አቀራረብ እየሆነ እንደመጣ ይገልፃል፡፡

ሁኔታ ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ የሰዋስው መማርና ማስተማር ተግባሩ የሚካሄደው አስቀድመን ስለ አዲሱ ሞዴል ገለፃ ከተደረገ በኋላ በዚያው መሠረት ልምምድ ያደርጋል፡፡ ሁኔታዊ አቀራረብን ስንጠቀም ሁኔታውን በጥንቃቄ በመቆጣጠር አዲሱን ቋንቋ እናስተምራለን፡፡ በዚህ ዘዴ ስናስተምር ተማሪዎች ስለ ሚሰሙት ነገር በአዕምሯቸው የሚፈጠር ምንም አይነት ትርጉም አይኖርም፡፡ ለመጀመሪያ ከአራት እስከ አምስት ዓመት ያህል ስለ ቃላት ቅርፅ ከተማሩ በኋላ በቀጣይ በተለያዩ በሁኔታዎች ውስጥ እነዚያ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ትርጉሙ በይበልጥ ግልፅ እየሆነላቸው ይሄዳል፡፡

Richards(1986: 34) እንደገለፀው ሁኔታ ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ በምንጠቀምበት ወቅት መምረጥ ያለብን ማስተማርያ መሣሪያዎች አብረው መኖር አለባቸው፡፡ እነዚህም ተጨባጭ የሆኑ ዕቃዎች፣ ስዕሎች እንድሁም እንቅስቃሴና ማነቋቂያ አብሮ መጠቀም የአዲሱን ቋንቋ ሰዋስው ትርጉም ለማስረዳት ይረዳል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ቅርፅና ዐ.ነገር ሞዴሎች በምሳሌ መሰረት ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለ ሰዋስው ገለፃና መግለጫ አያስፈለግም፤የአዳዲስ ቃላት ትርጉም እና የዐረፍተነገር ሞዴሎች የሚቀርበውም በመተርጎም አይደለም፤ ስዕሎች፣ ዕቃዎች በእንቅስቃሴ መታጀባቸው የበለጠ ግልፅ እንዲሆንላቸው ያደርጋል፡፡ ከሁኔታ ጋር የተያያዙ ጥሩ ሞዴል ዐረፍተ ነገሮች ወስደን በምንገልጽበት ወቅት ለተማሪዎች የበለጠ ግልጽ ይሆናል፡፡ በዚህ መንገድ ሰዋስውን እናስተምራለን፡፡ የሁኔታ ተኮር ማስተማር አቀራርብ ዋና መሠረት ያደርገው በመማሪያ መጻሕፍትና በሚታዩ የማስተማሪያ መሠሪያዎች ላይ ነው፡፡ ሁኔታ ተኮር አቀራረብ በከፍል ውስጥ ተግባራዊ ስናደርግ እንደየ ክፍል ደረጃቸው ይለያያል፡፡ ከክፍል ደረጃቸው ውጭ በሂደት በሁሉም ክፍል ደረጃ ተመሳሳይነት ይኖራቸዋል፡፡ መጀመሪያ ስለ ዓረፍተነገር መግለፅ ከዚያም በቀጥታ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ማንበብና መፃፍ እንዲለማመዱ ይደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ሁኔታውን በሚያስቡበት ወቅት ትርጉሙ ግልፅ እንዲሆንላችው ያደርጋል፡፡ ሌላው ይህ አቀራረብ ሰፋ ያለ የቋንቋ ከፍሎችን ለማስተማር ያግዛል፤ነገር ግን ሰፊ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎችን በአከባቢያችሁ ወደሚገኝ አንድ መዝናኛ ቦታ በመሄድ ስላያቹት ነገር የተለያዩ አረፍተነገሮችን መስርቱ ቢባሉ ሁኔታውን በሚያስቡበት ወቅት ትርጉሙ ግልፅ ሊሆንላቸው ይችላል ፡፡

## 2.1.5.3.1. ሁኔታ ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያት

የሁኔታ ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያትን Richards(1986) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ቋንቋውን ማስተማር የሚጀምረው በንግግር ቋንቋ ነው፡፡ ስለ አዲሱ ቋንቋ ገለፃ ከተደገ በኂላ በመቀጠል በሁኔታው ሙከራ ማድረግ፤ እንዲሁም ከቀለል ወደ ከባድ አደረጃጀትን መሰረት በማድረግ ሰዋስውን መሠረት ያደረገ ማንበብና መፃፍ ላይ በበቂ ሁኔታ ማመቻቸት ናቸው፡፡

## 2.1.5.4. ውጤት ተኮር አቀራረብ (PRODUCT BASED APPROACH)

ውጤት ተኮር አቀራረብ ማለት ቋንቋን በመማር በትክክለኛ መንገድ ለተግባቦት መጠቀም ማለት ነው፡፡ የዚህ አቀራረብ ዋና ትኩረት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ ቋንቋ ማስተማር ሂደት በሚመጣው ውጤት ላይ ሲሆን ለዚህ ተብሎ ተማሪዎች ትምህርቱን የሚጀምሩትም የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ከመለየት ነው፡፡ ይህ ማለት የትምህርቱን ይዘት

ለማስተማሪያ የተሰጠው ክፍለጊዜ ሲያጠናቀቅ ይህን ያውቃሉ ተብሎ ይታሰባል፤ ግቡን ለማሳካት የሚረዱ የማስተማር ስትራቴጂዎች ይመረጣሉ፡፡ እነዚህም፡- ፅሁፍ ተኮር ማስተማር(Text based instruction) እና ችሎታ ተኮር ማስተማር (competency-based instruction) ናቸው: Richards, (2006: 34).

## 2.1.5.4.1. ፅሁፍ ተኮር ማስተማር (TEXT BASED INSTRUCTION)

Richards (2006: 39) እንደሚሉት ፅሁፍ ተኮር ማስተማር አቀራረብ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ያተኮረ አቀራረብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ዕለት ተዕለት ተግባቦት ብቃቱን ለማሳደግ ሲል በሚደረገው ሂደት ውስጥ የተለያየ ዓይነት ቃላትን ያውቃሉ፡፡ ለተግባቦት ብቃት ሲል የተለያዩ ፅሁፍ በመጠቀም የተለያየ የቋንቋ አደረጃጀት ቅደም ተከተል ይመለከታል፤ ይህን የተመለከተውን በተወሰነ አውዶች ውስጥ በተወሰነ መልኩ ይጠቀማል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረበ አንድ ፅሁፍ ቢኖርና በዚያ ጽሁፍ ውስጥ ጸሐፊው በተለያየ አውድ የተነገሩ ንግግሮችን ተጠቅሞ ለመጻፍ በብዙ መንገድ ቋንቋን ሲጠቀም ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ ሰው በድንገት ከጓደኛው ጋር ሀሳብ ሲለዋወጥ፤ የሆነ ቦታ በመኪና ሲሄድ ከመንገደኛ ጋር ሀሳብ ሲለዋወጥ፤ፀጉር ቤት በስልክ ወረፋ ለማስያዝ ሲነጋገር፤በሰዎች ችግር ዙሪያ ከጓደኛ ጋር በመወያየት ምክር ለመስጠት ተጠቅሞ ለመጻፍ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ ይጠቀማል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ተናጋሪው የተጠቀመው ቋንቋ አንድ ቢሆንም የቋንቋ አጠቃቀሙ እንደየአውዱ ይለያያል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ፅሁፍ በክፍል ውስጥ በማቅረብ ስለተናጋሪው ወይም ስለተፃፊው ፅሁፍ ቅርጽና ሰዋስዋዊ ባህሪይ በግልጽ ማሰተማር ይረዳል፡፡ በተለያየ አውድ የቀረቡ ፅሁፎችን አቀናጅተን ስንሰጣቸው የተለያዩ ክህሎቶችን ያዳብራሉ፡፡

## 2.1.5.4.2. ብቃት ተኮር ማስተማር (COMPTENCY BASED)

ብቃት ተኮር ማስተማር አቀራረብ በሰፊው ጥቅም ላይ መዋል የጀመረው በ1970ዎቹ አከባቢ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ በስፋት እንዲጠቀሙ ያደረገው መሰረታዊ አቀራረቡ ከጎልማሶች ስራ አንጻር ውጤታማ ቋንቋ ማስተማር ፕሮግራም ለጎልማሶች ከሚለው ጋር የተያያዘ ስለነበረ ነው፡፡ Richards (2006: 34-40)፡፡ እነዚህ ጎልማሳ ተማሪዎች በዕለት ዕለት ህይወታቸው ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ለሚገጥማቸው የቋንቋ ክህል ችግር ለመቅረፍ መሰረታዊ የሆኑትን ክህሎች በተማሪዎቹ ፍላጎት ማስተማር ነው፡፡ ይህ በተለይ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ቋንቋን ለማስተማር በጥቅም ላይ ይውላል ፡፡

### 2.1.5.5. ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ (CONSEICUNEES RASING APPROACH)

ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ Widodo (2006: 126) & Ellis (2002:167) Richards & Platt (1992) እንደገለጹት ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ ማለት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ቅርጽ በዝርዝር ለመገንዘብ ሙከራ እንድያደርጉ ማነሳሳት ወይም ማዘጋጀት ማለት ነው። ይህ የሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ተማሪዎችን ሰዋስው በምናስተምርበት ጊዜ በሰዋስዋዊ ቅርጽ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እንደአንድ አነሳሽ (ቀስቃሽ) መንገድ ይጠቅማል።

Atkinns (2000: 4)። ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ሰዋስው በምናስተምርበት ወቅት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ቅርጽ ላይ ትኩረት እንድያደርጉ ማነቃቃት ይኖርብናል። በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ትርጓሜው ተማሪዎችን ሰዋስው ስናስተምር በማለማመድ፣ገለጻ በማድረግ፣ እንዲሁም የሰዋስው ቅርጽ ተኮር ተግባራት በማሳየት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ በሚመለከት የተማሪዎችን ግንዛቤ ማሳደግ ማለት ነው።ይህ በተዘዋዋሪ ቋንቋን እንዲለምዱ ማመቻቸት ማለት ነው። ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ ከጥንታዊ ሰዋስው ማሰተማር ዘዴ ጋርተመሳሳይነት አለው። የዚህ አቀራረብ ዋና ግቡ ትክክለኛ የሰዋስው ንድፍን በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ በመቅረጽ በቀጥታ ልምምድ እንድያደርጉ ማድረግ ነው።

ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ አዳዲስና ቀጣይነት ያላቸው የሰዋስው ህጎችን እንደሰንሰለት አያይዘው እንዲገነዘቡት በማድረግ ለዝርዝር ሰዋስዋዊ ክስተቶች ተጋላጭ እንድሆኑ ከማድረግ አንጻር ትልቅ ሚና ያለው የአቀራረብ ዘዴ ነው። Nassaji & Fotos (2011: 37) ::

Widodo (2006: 125) ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ ተማሪዎች የተወሰኑ የቋንቋውን ቅርጾች ማለትም የዐረፍተ ነገር ቅርጾች በራሳቸው ጥረት እንድያውቁ ማድረግ ነው። ነገር ግን ተማሪዎች የሚማሩት የግድ የዐረፍተ ነገር ቅርጽ እንዲያፈልቁ ወይም ቋንቋውን ለተግባቦት እንዲያውሉ ሳይሆን ተማሪዎች በሰዋስው ላይ ግልጽ ዕውቀት እንዲያዳብሩ ለማድረግ ነው።

### 2.1.5.5.1. ንቃተ ህሊና ቀስቃሽ አቀራረብ (CR) ባህሪያት

ንቃተ ህሊና ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ አበይት ባህሪያት Widodo (2006: 125) እንደሚከተለው ገልጸል ። የቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጽ በዝርዝር መለየት ላይ ትኩረት ያደርጋል፤ተማሪዎች የሰዋስው ቅርጽና ዝርዝር ህጎችን የሚያብራሩ መረጃ እንድያቀርቡ ፤ ተማሪዎች ስለሰዋሰው ቅርጽ የተሳሳተ ግንዛበ ካለቸው ለቀጣዩ በራሳቸው ተመራምረው እንዲደርሱበት እንዲያሻሽሉ እና የሰዋስውን ቅርጽ የሚገልጽ ህግ በራሳቸው እንዲናገሩ ያደርጋል።

## 2.1.5.6. ሂደት ተኮር (PROCESSES BASED APPROACH)

ሂደት ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ ማለት በተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማር አቀራረብ ውስጥ የሚካተት ሲሆን በውስጡ ሁለት ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ያደረገ አቀራረብ ነው። እነዚህም ይዘት ተኮር ማስተማር/content based instruction/ እና ተግባር ተኮር ማስተማር/task based instruction/ ናቸው። በዚህ አቀራረብ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማሳደግ ተግባቦታዊ ቋንቋ የማስተማር እንቅስቃሴ በማስፋት የተግባቦት ግብን ለማሳካት ተብሎ የተቀረጸ ስነ ዘዴ ነው።ሂደት ተኮር ሰዋስው ማስተማር አቀራረብ የሚያመለክተው ተመሳሳይ መነሻ ላይ ትኩረት በማድረግ በክፍል ውስጥ በሚደረግ ሂደት ቋንቋን በተሻለ መልኩ ለማስተማር የሚያመች አቀራረብ ነው ።

**ሀ ይዘት ተኮር ማስተማር/content based instruction/**

ይዘት ተኮረ ማስተማር ማለት የቋንቋውን ሰዋስው ይዘት በጥቂቱ ማስተማር፤ በተዘዋዋሪ ወይም በግልጽ ሰዋስውን ከቀረበው ቋንቋ ይዘት ውስጥ ለይቶ ማስተማር ማለት ነው።ዋና ትኩረቱም የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል በማሳደግ ሁለጊዜ ሰዋስውን በብቃት ማለፋቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው። Richards (2006: 46) እነዚህን ሂደቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተሻለ መልኩ ለመፍጠር ይዘትን ተጠቅመን ተግባርዊ በማድረግ ሲሆን በክፍል ውስጥ በተለያዩ መልክ በሚቀርቡ ተግባራት ውስጥ ሰዋሰው ያካተተ ይዘቱ አገናኝቶ ለማስተማር መጠቀም ማለት ነው።

Richards (2006) & Kranko (1987) እንደሚሉት ተግባቦት ቋንቋን በሂደት በመማር የምናገኘው ውጤት ነው። ሂደቱም በተማሪዎችና በቋንቋ ተጠቃሚ ህብረተሰብ መካከል ያለው መስተጋብር፤ለትርጉም አብሮነት የመፍጠር ፤በቋንቋ ዓላማና ትርጉም ያለው መስተጋብር የመፈጠር ፤ተማሪዎች መቼ ቋንቋውን መጠቀም እንዳለባቸው ከሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ ተከታትሎ የመማር ፤ለቋንቋው ትኩረት በመስጠት አዲስ ቅርጽ ለመፍጠርና

የተግባቦት ብቃት ለማሳደግ መሞከር እና በተለያየ መንገድ ነገሮችን ለመግለጽ ሙከራ የማድረግ ሂደት ነው።

## 2.2. መርሃ ትምህርት እና የቋንቋ የመማሪያ መጻህፍት

### 2.2.1. የቋንቋ መርሃ ትምህርት ምንነት

የአንድን የትምህርት ክፍል ደረጃ በየእርከን ደረጃው ተማሪ የሚማርባቸው አጠቃላይ የትምህርት ደረጃዎች፤ እንዴት መማር እንዳለባቸው ለምን በማን ምን መማር እንደሚገባቸው፤ እንዴት እንደሚመዘኑና እንደሚለኩ የሚያሳይ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ የአገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የትምህርት ፍልስፍና፣ የፖለቲካ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ጉዱዮች መነሻ አድረጎ የሚዘጋጅ ነው። ሰርአተ ትምህርት ሲዘጋጅ ተማሪወቹ እንዲደርሱ ከሚጠበቀው ግብ ላይ መመስረት ይኖርበታል (ETP, 1994: 12)::

Dubin and Olishtine (1986: 28) መርሃ ትምህርት የአንድ ተተኳሪ ትምህርት የክፍል ደረጃ ያገናዘበ መሪ እቅድ ወይም ዝርዝር እቅድ ነው። የቋንቋ መርሃ ትምህርት አንድ የተወሰነ የቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተማሪው ምን መማር እንዳለበትና መምህሩም ምን ማስተማር እንዳለበት የሚጠቁም መሳሪያ ነው። ይኸውም የቋንቋ ትምህርቱን አጠቃላዩንና ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች በምን ያህል መጠንና ጊዜ ማስተማር እንደሚገባና ተማሪዎቹም ምን ማወቅ እንደሚገባቸው ያመለክታል። እንዲሁም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የሚያመለክትና የሚመራ ነው። መርሃትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥ የሚረዳ ሰነድ ነው። የዓላማውን መሳካት ለማረጋገጥም ጠንካራውን ጎን በይበልጥ ለማጠናከር እንዲሁም ደካማውን ጎን ደግሞ ለማሻሻል የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያገለግሉ መስፈርቶችን በመጠቀም ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ ሰነድ ነው። የመርሃ ትምህርትን ምንነት Dubin and Olishtine (1991: 28) እንደሚከተለው ያብራሩታል።መርሃ ትምህርት ዝርዝርና ተተግባሪ የሆኑ የመማር ማስተማር አላባውያን እንዲሁም የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃላይ ፍልስፍና ወደ ተለያዩ የተግባር ደረጃዎች ከፋፍሎ ለማመለከት፣ ተስማሚ ይዘት ለመምረጥና ተገቢ ዓላማዎችን ነድፎ ለማስቀመጥ፣ የትኛው ይዘት በምን መሳሪያ፣ በማን እና በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት፣ ከቀረበም በኋላ እንዴት ሊገመገም እንደሚገባ ዝርዝር መረጃ የሚያቀርብ መጠነ ርዕዩ ጠባብ የሆነ፣ ለየትምህርት ዓይነቱና ለየክፍል ደረጃው የሚዘጋጅ ነው።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው መርሃ ትምህርት ለየትምህርት ዓይነቱና ለየክፍል ደረጃ የሚዘጋጅ እንደሆነ ነው። በተጨማሪም ተማሪው ምን መማር እንደሚገባውና መምህሩም ምን ማስተማር እንዳለበት የሚያሳውቅ ነው። የሥርዓተ ትምህርቱ መሣሪያዎች (ሲለበስ፣ የተማሪ መፅሐፍና የመምህሩ መምሪያ ማጣቃሻ መፃህፍት፣ የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች) ከተማሪዎቹ ዕድገት ደረጃና ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ፣ ከማናቸውም አድልዎ ነፃ የሆኑ ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ተገቢነት ያላቸውና የሚያሳትፉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር (2003: 13)

## 2.2.2. የመርሃ ትምህርት ፋይዳ

መርሀ ትምህርት እንድንነድፍ ከሚያስገድዱን ዋና ዋና ሁኔታዎች መካከል አበይት የሆኑትን ነጥቦች Hutchinson and Waters (1987: 83-84) & Dubin and Olishtine (1991) እንደሚከተለው ገልጸዋል።

ቋንቋ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ መግባቢያ መሳሪያ በመሆኑ ይህን ረቂቅና ውስብስብ የመግባቢያ መሳሪያ ተማሪው በአግባቡ እንዲማር መምህሩም በአግባቡ እንዲያስተምር ለማድረግ ረቂቁና ውስብስቡ ቋንቋ በጥልቀት ተመርምሮና ተሸንሽኖ ደረጃ በደረጃ ለትምህርት ሊቀርብ በሚችልበት መልኩ መቀመጥ ይኖርበታል። ይህ ደግሞ የመማሪያ መፅሐፉንና የመምህሩን መመሪያ ለማዘጋጀት እንዲሁም የማስተማሪያ መረጃዎችን ለማሰናዳት ትልቅ ጠቀሜታ አለው ።

መርሀ ትምህርት የቋንቋ ትምህርት እቅዱን ከመነሻው እስከመድረሻው ጥርት አድርጎ ስለሚያሳይ የቋንቋውን የትምህርት አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍ እንዲል ከማገዙም በላይ የቋንቋ ትምህርት ሂደት አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት እና ወደ ግብ መድረሻው መንገድ ይጠቁማል። እንዲሁም መርሀ ትምህርት የማስተማሪያ መጽሀፍ ለማዘጋጀትና የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን የሚይዝ ብቻም ሳይሆን ትኩረት ሊያገኝ የሚገባውን የመልመጃ አይነትም ጭምር በመጠቆም ረገድ ለቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛውን ዕገዛ ያደርጋል። በተጨማሪም መርሀ ትምህርት በአንድ ትምህርት ቤት፣በአንድ ከተማ፣በአንድ ክፍለሀገር ብሎም በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ ትምህርት ለመስጠትና የተማሪዎችን ውጤት ለመገምገም ያገለግላል። በስተመጨረሻም መርሀ ትምህርት ድህረ የቋንቋ ትምህርት ለሚደረገው ግምገማ መስፈርትና መነሻ ሆኖ ስለሚያገለግል የቋንቋው ትምህርት ሲጠቃለል

ለሚደረገው የግምገማ ወይም የምዘና ሂደት የመመዘኛውን ወይም የመገምገሚያውን መስፈርት በመጠቆም ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### 2.2.3. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትና የመርሀ ትምህርት ግኑኙነት

የቋንቋ መርሃ ትምህርት ከስራተ ትምህርት በታች ከመማሪያ መጻሕፍት በላይ በመሆን መጽሐፉና ስርዓተ ትምህርቱን የሚያገናኝ ነው፡፡ መርሀ ትምህርት መማሪያ መጻሕፍትና የመማር ማስተማር ሂደት የሚከተል ገዥ ሰነድ ነው፡፡

Rechards (1987) ስለ መማሪያ መጽሀፍትና ስለ መርሀ ትምህርት ግኙኙነት ሲገልጽ መማሪያ መጻህፍት በመርሀ ትምህርቱ ላይ በመመስረት ተዘጋጅቶ በመምህሩና በተማሪዎች አማካይነት በተግባር ላይ ይውላል፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መምህሩ ምን እንደሚያስተምር ተማሪውም እንዴት እንደሚማር መመሪያዎችም እንዴት ስራ ላይ እንደሚውሉ የሚያመለክት ሰነድ ነው በማለት ይገልጻል፡፡ ከዚህ በመነሳት መማሪያ መጻህፍትን መገምገም የሚቻለው በመርሀ ትምህርቱ መሰረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.2.4. የመምህሩ መምሪያና የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት

## 2.2.4.1. የመምህሩ መምሪያ ምንነት

የመምህሩ መምሪያ ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ እና መምህራን እንዴት እንደምያስተምሩ የሚያሳይ ሰነድ ነው፡፡ የመምህሩ መምሪያ መምህሩ ምን ማስተማር እንዳለበት እና እንዴት ማስተማር እንዳለበት ዝርዝር አቅጣጫ በማሳየት የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲሳካ ከማድረጉም በላይ ለመምህሩ ጽንስ ሀሳብን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እያዋሀደ የሚያስተምርበትን አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡ ለተማሪዎች ውጤታማ የቋንቋ አጠቃቀምን ለማስተማር ለመምህራን ተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ በማድረግ ረገድም ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን በመምህሩና በተማሪው መካከል እንደማግባቢያ ድልድይ በመሆንም ያገለግላል፡፡

Callison (2003: 31) እንደገለጸው የመምህሩ መምሪያ ለክፍል ውስጥ ትምህርት ማስተማሪያ እንደዋነኛ ግብዓት ይወሰዳል፡፡ የመምህሩ መምሪያ በተለይም ለመምህራንና ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ከማስተዋወቅ አንጻር በተቀናጀ ማዕቀፍ ውስጥ ለውጦችን ቀስ በቀስ ማሳወቅ ስለሚያስችል በትምህርት አቀራረብ ላይ ትልቅ ሚና አለው፡፡

Hutchinson & Torres (1994: 318) ይህን ሀሳብ ሲያጠናክሩት የመምህሩ መማሪያ ጊዜን ይቆጥባል፣ ለመምህራን እንዴት እንደሚስተምሩ መመሪያ ይሰጣል፣ ትምህርቱን ይመራል፣ ለመምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ መመሪያ እና ግንዛቤ ይሰጣል፤ ለመማሪያ መጽሀፍ ድጋፍ በመስጠት "በመማር ማስተማር ስርዓት የሚፈለገው ለውጥ እንዲመጣ መዋቅር ለማቅረብ በጣም ምቹ መንገዶች ይከፍታል፡፡ ሆኖም Powell & Alderson (2002: 317) የመምህሩ መማሪያ መፅሃፍ አጠቃቀም በትምህርታዊ እቅድ ማቀድ መምህሩን ማዕከል ያደረገ አቀራረብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ጥናትም እንደሚያሳየው የመምህሩ መማሪያ መጻሕፍ አጠቃቀም ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ይለያያል Sent-George ( 2001)፡፡ እንደገለጹት ባደጉት ሀገሮች ውስጥ በትምህርት ቤቱ ስርዓት ውስጥ የበላይነቱን ይይዛል፡፡ Quader (2001) & Alderson (1993: 16-17)፡፡ "የመምህሩ መማሪያ የመማሪያ መጻሕፍቱን ይዘት ተግባራዊ ለማድረግ፣ መምህራንን ለመምራት እና ይበልጥ ውጤታማ የማስተማር ዘዴን ለማቅረብ ተግባር ላይ ይውላል፡፡"

የመምህሩ መመሪያ ለመምህራን መመሪያዎችን ምሳሌዎችን ይሰጥና እነዚህን መመሪያዎችና ምሳሌዎች በክፍላቸው ውስጥ እንዴት እና ለምን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የመምህራንን አቅም በትምህርት ቤታቸው እና በክፍል ውስጥ በዓላማ እና በሙያ እንዲሠሩ ለመደገፍ ያግዛል፡፡

የመምህሩ መመሪያ በመብት ላይ የተመሠረተ እና ተማሪውን ማዕከል ያደረገ የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የመማር መብት እና ችሎታ አላቸው እናም በሁሉም ተማሪዎች ውስጥ መማር እና ተሳትፎን የሚያጎለብቱ የትምህርት አከባቢዎችን መፍጠር የትምህርት ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡ የመምህሩ መመሪያ ለአስተማሪዎች ተግባራዊ እውቀት እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በሌላ አገላለጽ በቀላሉ ወደ ተግባር የሚቀየር ዕውቀትን ይሰጣል፡፡ ይህንን ሂደት ለማመቻቸት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የተገለጋዩን አመለካከት በመጠቀም ይገለጻል፡፡ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴ አጠቃላይ እይታ ለተመሳሳይ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል- ለምን ይህ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ነው ዘዴዎች እና መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ ("እንዴት")

በአጠቃላይ እይታ የመምህሩ መመሪያ በሦስት ዋና ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል "ከመሰረታዊ መርሆዎች እስከ ትምህርትቤት-ተኮር ድርጊቶች"፡፡ ሁለተኛው ክፍል "ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ አቅም መገንባት" በክፍል ደረጃ ባሉ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡ በቅደም ተከተል ልምድ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ሦስተኛው እና የመጨረሻው ክፍል በተግባር ማዋል" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን የመምህሩ መምሪያ ተማሪውን በመማር ማስተማር ዝግጅት፣ አተገባበር እና ግምገማ ሂደት ውስጥ "ለምን" (ግቦችን

ማዳበር)፣ "ምን" (የሥርዓተ ትምህርት ይዘት እና ውክልና)፣ "እንዴት" (የመማር ማስተማር ስልቶች) እና "የት "(የመማር ማስተማር አከባቢዎች) የሚሉትን ጉዳዮች ይዳስሳል፡፡

## 2.2.4.2. የመምህሩ መምሪያ ምን ምን ነገሮችን ሊያካትት ይገባል

የመምህሩ መምሪያ ምን ምን ነገሮችን ሊያካትት እንደሚገባ Grossman & Thompson (2008: 2014-2026) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

ለመምህራን የፈጠራ ችሎታ ፍንጮችን የሚሰጡ መሆን አለበት፣ለመምህራንን የሚረዱ ጠቃሚ መመሪያዎችን በመስጠት ችሎታዎቻቸውን እና ሀሳቦቻቸውን እንዲጠቀሙ በማስቻል አዳዲስ እንቅስቃሴዎችን በመፍጠር ነባር ተግባራትን በፈጠራ መንገዶች እንዲጠቀሙ ማበረታታት ይኖርበታል፡፡ መምህራን መማሪያ መጽሀፉን ስልታዊ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ የሚያግዝ መሆን አለበት፡፡ የመምህሩ መመሪያ መምህራን ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ተማሪዎች እንዴት አካተተው ማስተማር እንዳለባቸው የሚያሳይ መመሪያ ሊኖረው ይገባል፤ ለመምህራን ለመምራት አመቺ የሆኑ የድምጽ ቅጅዎችን (አዶዎችን) የያዘ ሊሆን ይገባል ፤ ሆኖም እነዚህ በቁጥር መገደብና ወጥነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል እና በመግቢያ ገጾቹ ላይ መብራራት ይኖርባቸዋል ፡፡

እንዲሁም በመምህሩ መምሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ቋንቋ ከትምህርት ቋንቋው ጋር የሚስማሙና አቀራረባቸው ቀላል መሆን ይኖርበታል፤ በተጨማሪም ትምህርቱን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ይዘቶች ወይም መመሪያዎችን ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡

## 2.2.4.3. የመምህሩ መምሪያ ጠቀሜታ

UNICEF (2015) የመምህሩ የመምሪያ የመጠቀምን አስፈላጊነት እንደገለጹት የመምህሩ መምሪያ የመምህራንን ግንዛቤ በማስፋት በመማሪያ መጻህፍቱ ስለተካተቱ ይዘቶች የበለጠ እንዲረዱ እና እንዴት እንደሚያስተምሩ መንገዶችን በማሳየት እገዛ ከማድረጉም በላይ መምህራን በቀላሉ የመርጃ መሳሪያ እንዲዘጋጁ የትምህርቱን ይዘት እንዲያደራጁ ዝርዝር መመሪያን ይሰጣል፡፡ እንዲሁ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተሰጡትን ተግባራት እንዴት በማከናወን እንደሚቻል መመሪያ ይሰጣል ትምህርቱን ቀላል እና በተሻለ የተደራጀ ያደርገዋል፡፡ የትምህርት እቅዶችን የሚጠቀሙ መምህራን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ያሉትን እንቅስቃሴዎች እንዲገነዘቡ ለመደገፍ እና መምህራኖቹ የመማሪያ ዘዴን እንዲጠቀሙ ለማበረታታት የበለጠ እገዛ ያደርጋል፡፡

የመምህሩ የመምሪያ መምህራንን የበለጠ አዎንታዊ እንዲሆኑ ለማድረግ እና በተሻለ ለመደገፍ፤ተመሳሳይ ቋንቋን በመጠቀም በትምህርቱ ውስጥ መመሪያዎችን እና ይዘትን በአንድ ቦታ ላይ ወጥ ለማድረግ፤ለመምህሩ የትምህርቱን አቀራረብ ለማቅለል፤ለመምህሩ የሚያስተምረውን የይዘት መጠን ለመወሰን፤የትምህርት እቅዶችን ወይም የመማሪያ ማስታወሻዎችን ለማዘጋጀት ፤ መምህሩ እንዴት ማስተር እና መማሪያ መጻሀፉን እንዴት መጠቀም እንዳለበት ማብራሪያ በመስጠት አንድ ዓይነት( ወጥ የሆነ) አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ትምህርትን ታአማኒ ለማድረግ እና ጊዜን ለመቆጠብ ያገለግላል፡፡

## 2.2.5. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በቋንቋ መርሀ ትምህርት የተካተተውን ይዘት መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁና ተማሪው የሚጠበቅበትን የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያግዙ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ Brown (2000) እንደገለጸው የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በቋንቋ መርሀ ትምህርት የተካተተውን ይዘት መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁና ተማሪው የሚጠበቅበትን የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያግዙ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የመማሪያ መጻህፍት ተማሪው ቋንቋን በራሱ ጥረት ለተፈለገው አላማ እንዲጠቀምበት ወደሚያስችል ደረጃ የሚደርሱ አይነተኛ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የመማሪያ መፃህፍት መርሃ ትምህርትን መነሻ በማድረግ ሚዘጋጁ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በጽሁፍ ከሚቀርቡ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን በትምህርት ስርዓት ውስጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው የማስተማሪያ መርጃ መሳሪዎች ቀዳሚው ነው፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በግል፣ በቡድን፣ በመንግስት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ የመማሪያ መፃህፍት ሲቀረጽ የሚዘጋጅለትን የክፍል ደረጃ፣የተማሪዎችን ዳራ፣ የመምህሩና የአከባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

### 2.2.5.1. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ጠቀሜታ

Billows (1961) & Brown (1994) ስለቋንቋ መማሪያ ጠቀሜታ እንደሚከተለው ዘርዝረዋል:- ተማሪዎች በሚማሯቸው ይዘቶችና ክሂሎች መካከል የተመጣጠነ ነገር እንዲያገኙ ያደርጋል፤መረሀ-ትምህርቱን በተግባር ለመተርጎም ያስችላል፤ተስማሚ የቋንቋ አጠቃቀም ያቀርባል፤ለመምህሩ የሚያስተምረውን ቅደም ተከተል ይወስንለታል፤የትምህርቱን መነሻና መድረሻ ያሳውቃል፤መምህሩ በሌለበት ተማሪው በማንበብ ሊጠቀም ይችላል፤መምህሩ በየትኛው ይዘት ላይ ተዘጋጅቶ መግባት እንዳለበት

ያመልክታል፤ ለመምህሩ የሚያስተምረውን ቅደም ተከተል ለመወሰንና ለተማሪዎች ወጥ የሆነ እውቀት ለመስጠት ያገለግላል።

## 2.2.6. በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ (APPROACH)

አቀራረብ፡-ማለት ቋንቋን የመማርና ማስተማር ባህሪይ ግንኙነት ከግምት በማስገባት የተደለደለ አሰራር ማለት ነው። አቀራርብ በዝርዝር ስለቋንቋ መማር ያለው ደረጃ ማለት ነው። አቀራረብ ባስቀመጥነው ዘዴ መሰረት ስርዓት ባለው መንገድ የተደለደለ የአሰራር ሥርዓት ነው።

### 2.2.6.1. ግልጽነት

ለትምህርት የሚመረጥ ይዘት ምንም ያክል ትክክል ቢሆን ለተማሪው ሊገባ በሚችል መንገድ በግልጽ ካልቀረበ ትምህርቱ የታለመውን ግብ መምታት አይችልም። አንድ የትምህርት ይዘት ሲቀርብ ለተማሪው ግልጽ በሆነና ሊረዳው በሚችል መልኩ መቅረብ ይኖርበታል እንጂ ተማሪው ላይ ግርታ ሊፈጥር አይገባም። በተለይ ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፉን ከመማሪያ ክፍል ውጪም ስለሚጠቀሟቸው በመማሪያ መጽሐፉ የሚካተቱ ይዘቶች ግልጽ ሆነው መቅረብ አለባቸው። በመማሪያ መጽሐፉ የሚካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አሻሚ ሊሆኑ አይገባም። ስለዚህ ግልጽና በቀላሉ ለአረዳድ የሚመቹ መሆን ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን መልመጃዎች ተረድተው መስራት እንዲችሉ ትዕዛዞችና ማብራሪያዎች ግልጽ በሆነ መልኩ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

ተስፋዬ (1981: 94) የማስተማሪያ መሳሪያዎች የያዟቸው የትምህርት ይዘቶች መምህሩ እንድያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልጽ መስፈር አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው። ማስታሻዎችም እንደሁ ለተማሪዎች ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ ምንነታቸው በግልጽና በማያሻማ መልኩ እንዲቀርብ ያስፈልጋል። እንዲያውም በማስተማሪያዎቹ አማካይነት ለትምህርት የቀረበው ይዘት ጉዳይ ምንነትና የትምህርት አላማ ጭምር ግልጽ ሊሆኑ ይገባል።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ መካተት የሚገባቸው የሰዋስው ተምህርት ይዘቶች መልመጃዎች ግልጽነት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ነው። ይኸውም የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማዳበር መማሪያ መጽሀፉ ግልጽና ለመረዳት የሚያመቹ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ግልጽነት ሲባልም ቀላል የሆነ አገላለጽን በመጠቀም ተማሪዎቹ ያለ ምንም ግራ መጋባት ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ

የቀረበ ሊሆን ይገባል፡፡ መልመጃዎቹ ግልጽነት የጎደላቸውና ከተማሪዎቹ ግንዛቤና ችሎታ በላይ የሚፈታተኑ ዓይነት መሆን የለባቸውም፡፡ ስለዚህ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ዓላማውን ለማሳካት በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች(ምሳሌዎች፣ መልመጃዎች፣ ትዕዛዞች፣ ማስታወሻዎች ወዘተ) ግልጽ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ አብይ አላማ በ2014 ዓመተ ምህረት የታተሙት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፃህፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ በተተኳሪዎቹ መማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሃ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ ምን እንደሚመስል በመፈተሽ ጥናቱ ላነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የተቀመጠውን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ንድፍ ተግባራዊ ጥናቱ ተከናውኗል እንዲሁም ቅይጥ የምርምር (Mixed research) ጥናት አይነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

Fraenkel & Wallen (2014: 283) እና Gay, Geoffrey & Airasian (2012: 483) ቅይጥ ጥናት (Mixed research) ማለት በአንድ ጥናት ውስጥ ሁለት የምርምር አይነቶችን ማለትም አይነታዊ ምርምር (Qualitative research) እና መጠናዊ ምርምር( Quantitative research) አይነቶችን በአንድ ላይ አዋህዶ የመጠቀም ሂደት ነው፡፡ በአይነታዊ ወይም በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ብቻ ተጠቅመን ከምናገኘው ግኝት ይልቅ በሁለቱ ውህድ የምርምር አይነቶች ተጠቅመን የምናገኘው መረጃ ውጤት ጠንካራና ተአማኒነት ያለው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

እንዲሁም ይህ የቅይጥ ጥናት የተመረጠበት ምክንያት የጥናቱ አላማ በመማሪያ መጻሕፍቱ፣በመምህሩ መምሪያና በመርሀ-ትምህርቶቹ መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ በመሆኑ በምን ያክል ተጣጥመዋል የሚለውን በቁጥር፣በአሀዝና በመጠን ለማየትና በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍትና መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስሉ በገለጻ የቀረበ በመሆኑ ሁለቱም የምርምር አይነቶች በማስፈለጋቸው ነው፡፡

Creswell & Plano Clark, (2011: 544) እንደሚገልጹት አራት አይነት የቅይጥ ጥናት አይነቶች ያሉ ሲሆን ለዚህ ጥናት ተገቢ የሆነው ሲኬዌንሻል ኤክስፐላራቶሪ ዲዛይን(sequential exploratory research design) የተባለው የቅይጥ አይነት ነው፡፡ ይህ

የቅይጥ አይነት በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የሆነበት ምክንያት ከሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በመጠናዊም በአይነታዊም ከተሰበሰቡና ከተተነተኑ በኋላ ሁለቱን በማጣመር የመረጃው ውጤት የተገለጸ ሲሆን በአመዘኙ ግን በአይነታዊ የምርምር አይነት የተገለጸ ከመሆኑ አንጻር ይህ የቅይጥ አይነት ለዚህ ጥናት ተመራጭ ሆኗል፡፡

በመሆኑም አይነታዊ የምርምርን በመጠቀም በተተኳሪዎቹ መማሪያ መፃህፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት መርሃ ትምህርቶቹን መሠረት በማድረግ መቅረብ እና አለመቅረባቸውን፤ እንዲሁም ከሰዋስው ስነ-ትምህርት መርሆዎች አኳያ ምን እንደሚመስል በገላጭ የምርምር ስልት የሚቀርብ ሲሆን፤ በመማሪያ መጻህፍቱ፣ በመምህሩ መምሪያና በመርሀ-ትምህርቶቹ መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ ለማሳየት መጠናዊ ምርምር አይነት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 3.2. የጥናቱ ተተኳሪዎች

ጥናቱ በ2014 ዓ.ም በታተሙት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ በመሆኑ በመረጃ ምንጭነት ሰነዶች አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ እነዚህም ሰነዶች በ2014ዓ.ም ሲ/ብ/ህ/ክ/መ አማካኝነት ታትመው በስራ ላይ ያሉ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መምሪያ እና የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርቶች ናቸው፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በ2014 ዓ.ም በታተሙት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ሲሆን ለዚህ ጥናት አመቺ ሆኖ የተመረጠው ወሳኝ የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ወሳኝ ንሞና በውስጡ የተለያዩ አይነት የንሞና አመራረጥ ዘዴዎችን ያካተተ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አላማ ተኮር ንሞና (purposive sampling) በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

አላማ ተኮር ንሞና የተመረጠበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ በሁለተኛ እርከን ያሉ ክፍሎች ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ሲሆኑ የሁሉም ክፍሎች የመማሪያ መጻህፍትና መርሀ-ትምህርቶች በሙሉ በጥናቱ ውስጥ ቢካተቱ ካለው ጊዜ አንፃር ሊበዙና የጥናቱን አላማ ለማሳካት አስቸጋሪ ስለሚሆን፤ በመጀመሪያ ደረጃ በሁለተኛ እርከን ላይ ያሉትን የ7ኛና 8ኛ ክፍል ብቻ በዚህ ጥናት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት

የመማሪያ መጻህፍት ያልተመረጡት በሌሎች አጥኚዎች የተጠኑ በመሆናቸው ሲሆን የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ብቻ የተመረጠበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ 8ኛ ክፍል ላይ የሚሰጥ በመሆኑና ወደ ሁለተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩበት ድልድይ በመሆኑ በዚህ ክፍል ደረጃ በሚገኙ መማሪያ መጻሕፍት እና መርሀ-ትምህርቶች  ላይ ትኩረት ከመስጠት አንጻር በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡

የጥናት ዘመን አመራረጥን በተመለከተ 2014 ዓ.ም የተመረጠበት ምክንያት መጻህፍቱ ተሻሽለው የታተሙት በዚህ አመተ ምህረት በመሆኑ እና አሁን በስራ ላይ ያሉትም እነዚሁ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ ስለሆኑ ከዚያ በፊት ያሉትን መምረጡ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው፡፡

## 3.4. መረጃ መሰብሰቢያ

ማንኛውም አይነት ጥናት በሚካሄድበት ወቅት እንደ ምርምሩ አይነትና ባህሪ ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችለውን ሁነኛ መሳሪያ መምረጥ ይኖርበታል፡፡

እንደ ምርምሩ አይነት እንደተጠኝዎቹ ሁኔታ እንዲሁም እንደ አጥኚው ችሎታ ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቢኖሩም የዚህን ጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ ተገቢ የሆነው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆኑት በ2014 ዓ.ም የታተሙት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት  ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ስለሆነ የጥናቱን አላማ ከማሳካት አንፃር ሰነድ ፍተሻ ተመራጭ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኗል፡፡

## 3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በ2014 ተሻሽለው በታተሙት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማርያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ በመሆኑ ከተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት፣ከመምህሩ መምሪያ እና ከመርሀ-ትምህርቶች በሰነድ ፍተሻ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት በቅይጥ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት፣ በመምህሩ መምሪያ እና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በየንዑስ ክፍላቸው፤ ከስነ-ድምጽ ጀምሮ ስነ-ምዕላድ፣ ስነ-ሀረግ፣ ስነ-ፍቺና ስነ-አገባብ በማለት ተለይተዋል፡፡ በየንዑስ ክፍላቸው የተለዩት ይዘቶች አቀራረብ ከሰዋስው ትምህርት መርሆዎች አኳያ በትክክል መቅረብ አለመቅረባቸውን በመፈተሽ በገላጭ ስልት ተብራርቷል፡፡ እንዲሁም በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሰንጠረዥ፣በቻርት፣በቁጥር እና በመቶኛ ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጻህፍቱና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከመማሪያ መጻህፍት አደረጃጀት መስፈርት አኳያ ተተንትኗል፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱት አጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተሰጣቸው ትኩረት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ይዘት አኳያ ተተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በመርሀ-ትምህርቶቹ፣ በመማሪያ መጻህፍቱና በመምህሩ መምሪያ መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ በመጠን በቁጥርና በመቶኛና በቻርት ተተንትነው ቀርቧል፡

እንዲሁም በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት፣ በመምህሩ መምሪያና በመርሀትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሰዋስው ትምህርት መርሆዎች አኳያ እንዴት እንደቀረቡ ምሣሌዎችን በማቅረብ በገላጭ ስልት ተብራርቷል፡

# ምዕራፍ አራት

# 4. የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የመማሪያ መጻህፍቱ፣ የመምህሩ መምሪያ እና የመርሀትምህርቶቹ አጠቃላይ ገጽታ

የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ እንዲሁም የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰነዶች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ሲዳማ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ለክልሉ እንዲስማሙ ተደርገው የተዘጋጁ ሲሆን፣ በ2014 ዓ.ም.ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም. ስራ ላይ የዋሉ ናቸው፡፡ የ8ኛ ክፍል የተማሪው መጻሐፍ 255 ገጾች፣ የመምህሩ መምሪያ 149 ገጾች ሲኖሯቸው፣ የ7ኛ ክፍሉ 277 ገፅ፣ የመምህሩ መምሪያ ደግሞ 188 የገጽ ብዛት አላቸው፡፡ እንዲሁም መርሀ-ትምህርቶቹ በሁለት ወሰነ ትምህርት የተከፈሉ ሲሆን የ7ኛ ክፍሉ 19 ገጾች፣ ሲኖሩት የ8ኛ ክፍሉ 20 ገጾች አሉት፡፡

ተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍት አስር አስር ምዕራፎች ያሏቸው ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት ኖሮት አንዱ ምዕራፍ በሦስት ሳምንታት እና በዘጠኝ ቀናት ተከፋፍሎ እያንዳንዱ ምዕራፍ ስምንት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ በነበረው ሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ የሚቀረብበት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ትኩረት የተደረገባቸው የተተኳሪ መርሀትምህርቶች፣ መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት በክለሳ ድርሳናት በተነሱ ንድፈ ሃሳቦች ላይ በመደገፍ ተተትነዋል፡፡

በዚህ ጥናት ላይ ትኩረት ተሰጥቶባቸው የተተነተኑት ሰነዶች የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መምሪያና መርሀትምህርቶች ሲሆኑ በተተኳሪዎቹ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርት ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው ወይ? የሚለውን ምላሽ ለመስጠት በተለያዩ ሰንጠረዦች፣ ግራፎች እና ፓይ ቻርቶች አማካይነት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

McDonough & Shaw (1993: 13) የመማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያ መርሀ-ትምህርቱን መሰረት በማድረግ መርሀ-ትምህርቱ ላይ የሰፈረውን አላማና ይዘት ከግብ ለማድረስ የሚዘጋጁ ሲሆን ተገዢነታቸውም ለመርሀ ትምህርቱ ነው፤ ስለዚህ የመማሪያ

መጽሐፉና የመምህሩ መምሪያ ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቱ የመነጩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት በመምህሩ መምሪያና በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱት የስዋስው ትምህርት ይዘቶች በ7ኛ ና በ8ኛ ክፍል መርሀ ትምህርቶች ውስጥ በተካተቱ የስዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ መመስረት አለመመስረታቸውን በመተንተን ምን የህል ተጣጥመዋል የሚለውን ለማሳየት ከዚህ በታች ባሉት ሰንጠረዥች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.1፡- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍና መምህሩ መምሪያ በደረጃው ከተዘጋጀው መርሀትምህርት ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ**

| ተቁ | | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | በመርሃትምህት ውስጥየቀረቡ የሰዋስውትምህርት ይዘቶች | በመምህሩመምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | በመማሪያመጻሕፍ ውስጥየቀረቡየሰዋስው ትምህርት ይዘቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስነድምጽ | የድምጽ መጥበቅና መላላት | ✓ | ✓ | ✓ |
| 2 | ስነ ምእላድ | ቃላትን መነጠልና ማጣመር | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ተውሳከ ግስ ተውላጠ ስም | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃል መመስረት (ከቃል ክፍሎች አዳዲስ ቃላትን መፍጠር | ✓ | X | X |
| | | መደብ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃል መስራችና የእርባታ ምእላዶች | ✓ | X | X |
| | | ቃላትን በመዋቅር (በስርአት) መለየት | ✓ | X | X |
| | | እስርና ነጻ መዕላዶች | ✓ | X | X |
| | | የጊዜ ና የቦታ ተውሳከ ግስ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጊዜ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | መደብና ጊዜ መልካች ቅጥያ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የተውላጠ ስሞች እርባታ | ✓ | X | X |
| 3 | ስነ አገባብ | ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | አያያዦችን መጠቀም | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | አውንታዊ፣ አሉታዊ ዓረፍተነገር | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጥገኛ ዓረፍተነገር መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ውስብስብ ዓረፍተነገር መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጠቋሚ መስተአምሮች | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | መጠይቃዊ ዓረፍተነገር | ✓ | ✓ | ✓ |
| 4 | ስነ ፍች | የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍች | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ለቃላትአውዳዊ ፍች መስጠት | ✓ | ✓ | ✓ |

ከላይ ከለው ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት የስዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ በመማሪያ መጽሐፉና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አልፎ አልፎ በመርሀትምህርቱ ውስጥ ያሉ ነገር ግን በመማሪያ መጽሐፉና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያልተካተቱ ጥቂት ይዘቶች ተካተዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ምንም እንኳን ጥቂት ይዘቶች ያልተካተቱ ቢሆኑም በመማሪያ መጽሀፉና በመምህሩ መምሪያ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው ጥብቅ ቁርኝት እንዳላቸውና የተጣጣሙ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2፡- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍና መምህሩ መምሪያ በደረጃው ከተዘጋጀው መርሀትምህርት ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ**

| ተ.ቁ | | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | በመርሃትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | በመማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስነ - ድምፅ | | | | |
| | | ቃላትን መነጣልና ማጣመር | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የድምጽ መጥበቅና መላላት | ✓ | ✓ | ✓ |
| 2 | ስነ ምዕላድ | | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን በተለያየ ቅርጽ መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን በትክክል መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቅጥያ ምእላዶች | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን እያረቡ መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትና ቅጥያዎችን አጣምሮ መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ተውሳከ ግስ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጠቋሚ መስተአምር | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጊዜ አመልካች | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች | ✓ | ✓ | ✓ |
| 3 | ስነ አገባብ | | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ዓረፍተነገሮችን ወደ ጥገኛ ሀረግ መለወጥ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጥገኛ ሀረጎችን ከነጠላ ዓረፍተነገር ጋር | ✓ | ✓ | ✓ |


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ማያያዝዓረፍተነገር መመስረት | | | |
| | | ዓረፍተ ነገርን ማስተከከል | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ዓረፍተ ነገርን መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የማስሪያ አንቀጽን ሙያ መለየት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ነጠላ አረፍተነገሮችን በማቀናጀት ድረብ ዓረፍተነገር መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | መጠቃዊ ዓረፍተ-ነገሮችን መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | በዓረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎች ሙያ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | አውንታዊ አረፍተ-ነገሮችን ወደ አሉታዊ መለወጥ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተ-ነገሮችን መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተ-ነገር መመስረት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላት ሀረጋትና ዓረፈተ-ነገሮችን በትክክል መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጥገኛ ሐረጎችን መለየት | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | ጥገኛሐረጎችን፣ ነጠላ ዓ.ነገሮችን እና ስማዊ ሀረጎችን መለየት | ✓ | ✓ | ✓ |
| 4 | ስነ ፍች | | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ ፍቺ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ | ✓ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ | ✓ | ✓ | ✓ |

ከላይ ከላው ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት የስዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ተካተው ቀርበዋል፡፡ይህ የሚያሳየው መማሪያ መጻህፍቱና የመምህሩ መምሪያ ሲዘጋጅ መርሃ ትምህርቶቹን መነሻ አድርገው መዘጋጀታቸውን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ይዘቶች ተካተዋል ማለት በመጠንም አንድ ናቸው ማለት አይደለም ይህንን በስፋትና በዝርዝር ቀጥሎ ባሉት ሠንጠረዦች ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 4.3 ፡- የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መርሀትምህርቶች ውስጥ የተካተቱ ንኡሳን የሰዋስው ይዘቶች በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | የሰዋስው ትምህርት ንዑሳን ይዘቶች | የ7ኛ ክፍል መርሃትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | የ8ኛ ክፍል መርሃትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | ጠ/ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስነ -ድምፅ | 1 | 2.6 | 1 | 3.6 | 2 | 3. |
| 2 | ስነምዕላድ | 18 | 47.4 | 9 | 32.1 | 27 | 41 |
| 3 | ስነ አገባብ | 13 | 34.2 | 13 | 46.5 | 26 | 39.3 |
| 4 | ስነ ፍች | 6 | 15.8 | 5 | 17.8 | 11 | 16.7 |
| | ድምር | 38 | 100 | 28 | 100 | 66 | 100 |


ፓይ ቻርት 4.1፡- የ7ኛ ክፍል መርሃ-ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች




ከላይ ከቀረበው ፓይ ቻርትና ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ7ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 18 (47%) በመቀጠል ስነአገባብ 13(34%) ስነፍቺ 6(16%) ዝቅተኛው

የሰዋስው ይዘት ስነድምጽ 1(3%) በመሆን ተካተዋል፡፡ ስለዚህ በሰባተኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥ ካሉ ንኡሳን ይዘቶች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን ዝቅተኛው ስነድምጽ ነው፡፡እንዲሁም በጠቅላላው በ7ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥ ከስነድምጽ እስከ ስነፍቺ 38 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

**ፓይ ቻርት 4.2፡- የ8ኛ ክፍል መርሃ-ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**





ከላይ ከቀረበው ፓይ ቻርትና ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነአገባብ ሲሆን 46% በመቀጠል ስነምዕላድ 32% ስነፍቺ 18% ዝቅተኛው የሰዋስው ይዘት ስነድምጽ 4% በመሆን ተካተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በ7ኛና 8ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱ ንኡሳን ይዘቶች በአጠቃላይ 66 ሲሆኑ ስነምዕላድ 27፣ስነአገባብ 26፣ ስነፍቺ 11 እና ስነድምጽ 2 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከቀረበው ፓይ ቻርትና ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በሁለቱም የክፍል ደረጃ ከቀረቡት መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ ከስነድምጽ እስከ ስነፍቺ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተካተቱ መሆኑንና ከፍተኛውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የያዘው ስነምዕላድ እንዲሁም ዝቅተኛውን ቁጥር የያዘው ስነድምጽ መሆኑን ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 4.4 ፡- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍና መምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ንሱሳን ይዘቶች**

| ተ.ቁ | የሰዋስው ትምህርት ንዑሳን ይዘቶች | በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡየሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | በ7ኛ ክፍል መምህሩ መምሪያውስጥየቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | ጠ/ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስነ -ድምፅ | 1 | 1.4 | 1 | 1.5 | 2 | 1.5 |
| 2 | ስነምዕላድ | 28 | 38.4 | 22 | 34.4 | 50 | 36.5 |
| 3 | ስነ አገባብ | 24 | 32.8 | 21 | 32.9 | 45 | 32.8 |
| 4 | ስነ ፍች | 20 | 27.4 | 20 | 31.2 | 40 | 29.2 |
| | ድምር | 73 | 100 | 64 | 100 | 137 | 100 |


**ግራፍ 4.1፡- በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**




ከላይ ከቀረበው ኮለን ቻርት እና ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 28(38.4%) በመቀጠል ስነአገባብ 24(32.4%) ስነፍቺ 20(27.4%) ዝቅተኛው የሰዋስው ይዘት ስነድምጽ 1(1.4%) በመሆን ተካቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው በ7ኛ

ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ሁሉም ንኡሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካተታቸውን እንዲሁም ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ንኡስ ይዘት ስነምዕላድ መሆኑንና ዝቅተኛውን የሰዋስው ይዘት የያዘው ደግሞ ስነድምጽ መሆኑን ነው፡፡

**ግራፍ 4.2፡-በ7ኛ ክፍል መምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**





ከላይ ከቀረበው ኮለን ቻርት እና ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ7ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 28(34.4%) በመቀጠል ስነአገባብ 21(32.9%) ስነፍቺ 20(31.2%)ስነድምጽ1(1.5%) በመሆን ተካቷል፡፡ በአጠቃላይ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ እና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቅላላ 137 ሲሆኑ ስነምዕላድ 50(36.5%)፣ስነአገባብ 45(32.8%)፣ ስነፍቺ 40(29.2%) እና ስነድምጽ 2(1.5%) ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 4.5 ፡- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍና መምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ንሱሳን ይዘቶች በቁጥርና በመቶኛ**

| ተ.ቁ | የሰዋስው ትምህርት ንዑሳን ይዘቶች | በ8ኛክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥየቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | በ8ኛክፍል መምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | ጠ/ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስነ -ድምፅ | 1 | 1.4 | 1 | 1.7 | 2 | 1.6 |
| 2 | ስነምዕላድ | 26 | 36.6 | 20 | 33.3 | 46 | 35.1 |
| 3 | ስነ አገባብ | 20 | 28.2 | 21 | 35 | 41 | 31.3 |
| 4 | ስነ ፍች | 24 | 33.8 | 18 | 30 | 42 | 32 |
| | ድምር | 71 | 100 | 60 | 100 | 131 | 100 |


**ግራፍ 4.3፡- በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**




| | ስነ ድምጽ | ስነ መዕላድ | ስነ አገባብ | ስነ ፍቺ |
|---|---|---|---|---|
| Series1 | 1.4 | 36.6 | 28.2 | 33.8 |

ከላይ ከቀረበው ባር ቻርት ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ንኡሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 26(36.6%) በመቀጠል ስነፍቺ 24(33.8%) ስነአገባብ 20(28.2%) ዝቅተኛው የሰዋሰው ይዘት ስነድምጽ1 (1.4% )ያህሉን ይሸፍናል፡፡ይህ የሚያሳየው በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ሁሉም ንኡሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካተታቸውን እንዲሁም ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ንኡስ ይዘት ስነምዕላድ መሆኑንና ዝቅተኛውን የሰዋስው ይዘት የያዘው ደግሞ ስነድምጽ መሆኑን ነው፡፡

**ግራፍ 4.4፡- በ8ኛ ክፍል መምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች**




ከላይ ከቀረበው ባር ቻርት እና ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 42(33.3%) በመቀጠል ስነአገባብ 46(35%) ስነፍቺ 41(30 %)ዝቅተኛው የሰዋሰው ይዘት ስነድምጽ 2(1.7 %) ያህሉን ይሸፍናል፡፡ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሐፍና መምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በጠቅላላ 131 ሲሆኑ ስነምዕላድ 46፣ስነአገባብ 41፣ስነፍቺ 42 እና ስነድምጽ 2 ናቸው፡፡ ስለዚህ በሁለቱም የመምህሩ መምሪያና መማሪያ መጻሐፉ ውስጥ ከፍተኛው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ስነምዕላድ ሲሆን ዝቅተኛውን ቁጥር የያዘው ስነድምጽ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4.6 ፡- የ7ኛና8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍና መምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ንሱሳን ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ

| የሰዋስው ትምህርት ንዑሳን ይዘቶች | 7ኛና8ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | በ 7ኛ ና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነ -ድምፅ | 2 | 3 | 4 | 2 |
| ስነምዕላድ | 27 | 41 | 96 | 35.5 |
| ስነ አገባብ | 26 | 39.3 | 86 | 32.5 |
| ስነ ፍች | 11 | 16.7 | 82 | 30 |
| ድምር | 66 | 100 | 268 | 100 |

በአጠቃላይ በመማሪያ መጻህፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስነምዕላድ 35.5%፣ስነአገባብ 32.5%፣ስነፍቺ 30% እና ስነድምጽ 2 ሲሆን በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ከቀረቡት ደግሞ ስነምዕላድ 41%፣ስነአገባብ 39.3%፣ስነፍቺ 16.7% እና ስነድምጽ 3 %ናቸው። ስለዚህ በሁለቱም የመምህሩ መምሪያ፣ መማሪያ መጻህፍቱና መርሀ-ትምህረቶቹ ውስጥ ከፍተኛውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን ዝቅተኛውን ቁጥር የያዘው ደግሞ ስነድምጽ ነው። እንዲሁም ሌሎች ስነአገባብና ስነፍቺም ተቀራራቢ ይዘት አላቸው። ስለዚህ በመቶኛ የተሰሉት ውጤቶች እንደሚያሳዩት በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ተመጣጣኝ ውክልና ያላቸው መሆኑ በመጻህፍቱና በመርሀ-ትምህርቶቹ መካከል ጥብቅ የሆነ ተጣጥሞሽ እንዳለ መረዳት ይቻላል።

## 4.2. መማሪያ መጽሀፍቱ፣ በመምህሩ መምሪያ እና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1. የሰዋስው ትምህርት ከግልጽነት አንጻር

በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው አንድ የትምህርት ይዘት ሲቀርብ ለተማሪው ግልጽ በሆነና ሊረዳው በሚችል መልኩ መቅረብ ይኖርበታል እንጂ ተማሪው ላይ ግርታ ሊፈጥር አይገባም፡፡ በተለይ ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፉን ከመማሪያ ክፍል ውጪም ስለሚጠቀሚቸው በመማሪያ መጽሐፉ የሚካተቱ ይዘቶች ግልጽ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍቱም ሆነ በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አሻሚና አጠራጣሪ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ስለዚህ ግልጽና በቀላሉ ለአረዳድ የሚመቹ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ሰነዶች የሰዋስው ትምህርትን ግልጽ አድርጎ ከማቅረብ አንጻር ሲፈተሹ አብዛኞቹ ይዘቶች ግልጽ ሆነው ቢቀርቡም አልፎ አልፎ በመልመጃዎች፤ በምሳሌዎች፤ በመመሪያዎች ላይ የታዩ የግልጽነነት ችግሮች ያለባቸውን ይዘቶች እንመልከት፡፡

ከማስታወሻ ግልጽነት አንጻር ለምሳሌ፡- (7ኛ ክፍል ገጽ 70) "…ከግስ በፊት ገብቶ ግስን የገለጸ ሁሉ ተውሳከግስ ሳይባል ይችላል፡፡ ተውሳከግሶች ግስን የሚገልጹት ከጊዜ፣ ከቦታ፣ከሁኔታ ወዘተ አንጻር ነው፡፡" ይላል ነገር ግን ከግስ በፊት ገብቶ ተውሳከግስ ያልሆነ ቃል በማምጣት ለምን ተውሳከግስ እንዳልሆነ በምሳሌ ማስረዳት ነበረበት እንጂ እንዲሁ በደፈናው ከግስ በፊት የገባ ሁሉ ተውሳከግስ አይደለም መባል የለበትም፡፡ ትዕዛዙ ላይ ስንመጣ "ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢውን ተውሳከግስ በመጻፍ አገልግሎቱን ግለጹ፡፡" ይላል በትዕዛዙ ውስጥ በክፍት ቦታዎቹ ሊገቡ የሚችሉ አማራጭ ተውሳከግሶችን ማስቀመጥ ነበረበት፤ አለበለዚያ ግን በክፍት ቦታው የሚያስገቧቸው ቃላት ተውሳካግስ ስለመሆናቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

ለምሳሌ፡- ልጆቹ------------------------- ናቸው፡፡ ይላል በዚህ ክፍት ቦታ መጥፎ፣ ክፉ፣ ቤት፣ ሁለት፣ ቆንጆ ወዘተ ቃላትን በዚህ ክፍት ቦታ ማስገባት ይቻላል፡፡ እነዚህ ቃላት ተውሳከግስ ይሁኑ አይሁኑ ተማሪዎቹ በግልጽ ላያውቁ ይችላሉ፡፡

ይህ ችግር በተመሳሳይ በመምህሩ መምሪያ ለይም በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ (7ኛገጽ 46) ላይ ተውሳከግሶች ከግስ በፊት እየገቡ ግስን እንደሚገልጹ ከመንገር ውጪ ከግስ በፊት የገባ ሁሉ ተውሳከግስ ማይሆንበትን ምክንያት ለማስረዳት አይሞክርም፡፡

(7ኛ ገጽ164) በመርሀትምህርቱ ላይ ግን የጊዜና የቦታ ተውሳከግሶችን ይለያሉ፡፡ ይላል ስለዚህ የጊዜና የቦታ ተውሳከግሶች የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ በዝርዝር በመማሪያ መጻህፉ ላይ መገለጽ ነበረበት ነገር ግን አልተገለጸም፡፡

(8ኛ ገጽ44) ትዕዛዙ "ቅጥያዎችን ከቃላት መነጠል፡፡" ይላል

ለምሳሌ፡- **ጎልማሳነት**

**ጎልማሳ-ነት** ሲሆን **እየተከተላችሁ** የሚለው ደግሞ **እየ-ተከተላ-ኣችሁ** ብለው ሊከፍሉት ነው **ተከተላ** ደግሞ ትርጉም የለውም፤ **እየ-ተከተል-ኣችሁ** ብለው እንዳይከፍሉት ስለድምጸልሳናት አቀነጃጀት የተሰጣቸው ትምህርትም ምሳሌም የለም፡፡ በዚህን ጊዜ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ልጆች ሊወዛገቡ ይችላሉ፡፡

(8ኛ ገጽ45) **ርቆ-ብ-ኣችሁ-ኣል** በዚህ ቃል ላይ ካሉት ቅጥያዎች መካከል ቅጥያ **ብ** በተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ አገልግሎቷ ግልጽ አይደለም፡፡ አብዛኞቹ በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉት ቅጥያ ምዕላዶች ቁጥርን፣ ጾታን፣ ባለቤትነትን፣ ተሳቢነትን ጊዜን የሚያመለክቱ ሲሆኑ እንደነ **ብ** አይነት ቅጥያዎች አገልግሎታቸው ግልጽ አይደለም፡፡

እንዲሁም (8ኛ በገጽ 67) **ፍላጎታቸውን** ሲነጣጠል **ፍላጎት-ኣቸው-ን** ተብሎ ተከፍሏል፤ ሌላ ቦታላይ ደግሞ (8ኛ በገጽ 61) **በተሰማራችሁበት** ሲነጣጠል **በ-ተ- ሰማር-ኣችሁ-ብ-ት** ተብሎ ተነጣጥሏል፤ በዚህ አከፋፈል መሠረት **ፍላጎታቸውን** የሚለውን **ፍላግ-ኦት-ኣቸው-ን** ተብሎ መከፈል ነበረበት፡፡ 7ኛክፍል መምህሩ መምሪያ ውስጥ(ገጽ 61) ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር ላይ ምሳሌ ሲሰጥ **ትምህርታቸውን ትምህርት-ኣቸው-ን** ብሎ ምሳሌ ከሰጠ በኋላ ቀጥሎ ያለው **ኢትዮፒክስ ኢ-ት-ዮ-ፒ-ክ-ስ** ተብሎ ተነጣጥሏል፡፡ ይህ በአንድ ትእዛዝ ላይ ሁለት አይነት አሰራር ተማሪውን ያወዛግባል የመጀመሪያው በነጻ ምዕላድና በጥገኛ ምዕላድ የተከፈለ ሲሆን ሁለተኛው ግን እንዴት እንደተከፈለም ግልጽ አይደለም፡፡

እንዲሁም በገጽ55 **የሚያስቃያቸውን** ተነጣጥሎ ሲጻፍ **የሚያስቃዩ-ኣቸው-ን** ተብሎ ምሳሌ ተሰጥቷል መሆን የነበረበት ግን **የም-ኢ-ኣስቃይ-ኣቸው-ን** ተብሎ መጻፍ ነበረበት፡፡ ያ የተከሰተቸው ሁለቱን አናባዎች ለማስወገድ ነው፡፡ በአማርኛ ሁለት አናባዎች ተከታትለው ሲመጡ ወደ ው ወይም ወደ ይ ይቀየራሉ፡፡

በአጠቃላይ በአብዛኛው ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር ላይ በመምህሩ መምሪያም ሆነ በመማሪያ መጻሕፍቱ የመምሪያም እና የምሳሌዎች ግልጽነት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ቃላቱ ሲነጣጠሉ በነጻና ጥገኛ ምዕላዶች ይሁን በድምጸ-ልሳን ይሁን በየትኛው መንገድ እንደሚነጣጠሉ የተቀመጠ ግልጽ ትእዛዝ የለም፡፡ እንዲሁም በአንድ ትእዛዝ ውስጥ ሁለት

አይነት አሠራረሮች በተደጋጋሚ ይታያሉ፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎቹ ላይ የእውቀት ክፍተት እንዲፈጠርና በትምህርቱ ላይ እርገጠኛ  እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

### 4.2.2.የሰዋስው ትምህርት ከትክክለኝነት አንጻር

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ትክክለኛና ከስህተት የጸዱ ግብአቶችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ይዘትም የቋንቋውን እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ስነልሳናዊ በህሪይ  የሚያሳይና የቋንቋ ተናጋሪው ህብረተሰብ የሚጠቀምበት ሊሆን ይገባል፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲማሩት የነበረውን ሰዋስዋዊ ይዘት ከውጭ ባለው በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ መካከል ልዩነት እንዳይፈጠር ያደርጋል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸው አብዛኖቹ ትክክለኛነት ያላቸው ሲሆኑ ጥቂት ትክክለኛነት የጎደላቸውን የሰዋስው ይዘቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

**ምሳሌ**፡-ለ/ ከድጃ ትምህርት ቤት **መጣች** ግን ክፍል ውስጥ አልገባችም፡፡ ይላል፡፡ (7ኛ ገጽ8) መሆን የነበበረበት ግን ከድጃ ትምህርት ቤት **መጥታለች** ነገር ግን ክፍል ውስጥ አልገባችም፡፡ የሚል ቢሆን ከመጀመሪያው በተሻለ ስሜት ይሰጥ  ነበር ስለዚህ አረፍተነገሩ ስህተት አለበት፡፡

መ/ ጅብሪል ድርሰት ጻፈና ለህትመት አበቃ፡፡

ረ/ ከድር የተፈጥሮ አከባቢን ማድነቅ ይወዳል ኤደን ግን ልቦለድ ጽሁፎችን ማንበብ ትወዳለች፡፡ (7ኛ ገጽ8)

አረፍተነገሮቹን ለማያያዝ የገባው ቃል **ግን** ትክክል አይደለም **ግን** የሚገባው መጀመሪያ የመጣውን ሀሳብ ወይም ዓ.ነገር ለማፍረስ ነው እንጂ የሚገባው የመጀመሪያውን ለማጠናከር አይደለም ፤ መሆን የነበረበት ከድር አከባቢያዊ ተፈጥሮን ማድነቅ ይወዳል፤ ኤደን ደግሞ የልበለድ ጽሁፎችን ማንበብ ትወዳለች፡፡ቢሆን የተሻለ  ነበር፡፡

**ምሳሌ**፡- አያያዦችን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡ (7ኛ ገጽ 20) ከሀ-መ ያሉት ትክክል ሆነው **ሠ** ላይ ግን አረፍተነገሩ ከነባራዊ እውነታ የራቀ ነው፡፡

ሠ/ ሀሊማ በጥሩ ሁኔታ አጠናች፡፡

ሀሊማ ፈተናውን አላለፈችም፡፡

እነዚህ አረፍተነገሮች ድርብ አረፍተነገር ሆነው ሲመሰረቱ **ሀሊማ በጥሩ ሁኔታ አጥንታለች ነገር ግን ፈተናውን አላለፈችም፡፡** ይሆናል ይህ ደግሞ ትክክል አይደለም ምክንያቱም

አንድሰው በርትቶ ካጠና ፈተናውን የማያልፍበት ምክንያት የለም፡፡ ለተማሪዎቹም ጥሩ ምሳሌ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ከእውነተኛው አለም ጋር የማይገናኝ ነው፡፡ ይህ ችግር በመምህሩ መምሪያ ላይም ይታያል፡፡7ኛ ገጽ 23 ፋጡማ ኀበዝ ናት ነገርግን ፈተናውን አላለፈችም፡፡ ይላል ስህተቱ ተመሳሳይ ነው፡፡

ሌላው "የሚከተሉትን አረፍተነገሮች አውንታዊ ወይም አሉታዊ እያላቹ መድቡ፡፡" (8ኛ ገጽ 23) ይላል ትእዛዙ ነገርግን መልመጃዎቹ የቀረቡት በአውንታዊ ወይም አሉታዊ ብቻ አይደለም፡፡ አስቲ ቀጥሎ የቀረቡትን መልመጃዎች እንመልከት፡-

ሀ. ጠንካራ የስራ ባህል ማህበራዊ እድገት ያመጣል፡፡

ለ. በጥገኝነት መኖር አያዋጣም፡፡

ሐ. ደቦ ለምን ይጠቅማል?

መ. የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት የስራ እድል ይፈጥራል፡፡

ሠ. ሰዎች ካልሰሩ ምን ይሆናሉ?

ከላይ ከቀረቡት መልመጃዎች መካከል ሀ፣ለ እና መ በአውንታዊ እና አሉታዊ የቀረቡ ሲሆን ሐ እና ሠ ግን መጠይቃዊ አረፍተነገር ናቸው፤ መጠይቃዊ አረፍተነገር ደግሞ በትእዛዙ ውስጥ የለም፡፡

(7ኛ ገጽ100) ደን በማልማት የአየር ሞቃትነትን መቀነስ ይቻላል------------- **ደን** ከመቁረጥ አልተቆጠበም፡፡ በዚህ አረፍተነገር ላይ ያለው ችግር በክፍት ቦታው ላይ **ነገር ግን** የሚል ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ **ደን** የሚለው ስም ላይ ተሳቢ አመልካች **ን** ባለመግባቱ አረፍተነገሩ ስሜት አጥቷል፤ **ደንን** መባል ነበረበት፡፡ **ይቻላል** ከሚለው ቀጥሎ **ሕብረተሰቡ** የሚል ባለቤት ሊኖረው ይገባል፡፡ስለዚህ አረፍተነገሩ የትክክለኛነት ችግር አለበት፡፡

(7ኛ ገጽ6) በመምህሩ መምሪያ ላይ አልማዝ ቦርሳዋን አስቀመጠችና ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡ በሚለው አረፍተነገር ውስጥ አያያዥ ሆኖ የገባው **ና** ነው፡፡ መልስ ነው ተብሎ የተቀመጠው ደግሞ እና ነው ይህ ተማሪዎችን ያወዛግባል፡፡

(8ኛ ክፍል ገጽ 38) ቃላትን መጣመርና መነጣጠል የሚለው ላይ **እንደተገነዘብነው** ሲነጣጠል **እንደ-ተገነዘብነው** ተብሎ ተቀምጧል መጻፍ የነበረበት **እንደ-ተገነዘብ-ነው** ተብሎ ነበር፡፡

(8ኛ ክፍል ገጽ 61) ተነጣጥለው የተጻፉትን ቃላት እንደገና አጣምራችሁ ጻፉ፡፡

ሐ/ አ-ድንቅ-አው-ል-ኣት- ኣል

ረ/ አብልተው-ኣቸው-ኣል

ሐ እና ረን ስንመለከት አንዳይነት ቅርጽ እያላቸው ግን ሁለቱም የተለያየ አከፋፈል ነው ያላቸው፡፡ይሄ ደግሞ ወጥነት ስሌለው ተማሪዎችን ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

እንዲሁም በመምህሩ መምሪያ ውስጥ (7ኛ ክፍል ገጽ19) መስተዋድድ በሚል ይዘት ስር የተሰጠ ማስታወሻ "መስተዋድዶች ከሌሎች ቃላት ጋር ካልተጣመሩ በስተቀር በተናጥል ትርጉም የሌላቸው ሲሆን የሚቀናጁትም ደግሞ ከስም ወይም ከግስ ጋር ነው፡፡" ይልና ከግስ ጋር እንዴት እንደሚቀናጅ ካሳየ በኂላ ከስም ጋር እንዴት እንደሚቀናጅ የሰጠው ማብራሪያ የለም፡፡ በአጠቃላይ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩት ይዘቶች የትክክለኛነት ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች እንዲያውቋቸው የሚፈለገውን የሰዋስው ዕውቀት የተዛባ እንዲሆን፣ እንዲሁም ከእውነተኛው አለም ጋር የማይገናኝና ተጨባጭነት የሌለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 4.2.3. የሰዋስው ትምህርት ከተገቢነት አንጻር

Sheldon (1988:237) ተገቢነት ያላቸው የሰዋስው ይዘቶች ከተማሪዎቹ ደረጃ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ስለሚጣጣሙ ተማሪዎች በቀላሉ እንዲረዷቸው ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በተማሪዎች ዘንድ ግርታና የመሰላቸት ሁኔታ እንዳይፈጠር ይረዳል፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ችሎት፣ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ተጣጥመው መቅረብ አለባቸው እንጂ ከተማሪዎቹ የመገንዘብ አቅም በላይ ከባድ ሆነው መቅረብ የለባቸውም፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች አብዛኞቹ ተገቢነት ያላቸው ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ለቀረቡበት የክፍል ደረጃ የሚከብዱ ሆነው የተገኙትን ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡-ጠቋሚ መስተአምርና ስምን አንደ መሙያ የያዙ ስድስት አረፍተነገሮች መስርቱ፡፡ (7ኛ ገጽ 62) ይላል፡፡ ይህ ትዕዛዝ ያለምንም ምሳሌና ማብራሪያ የቀረበ በመሆኑ ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ይከብዳል፡፡

ምሳሌ፡-ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር አጣምሮ መጻፍ፡፡ **ትክክልኛ** ይላል ሌሎችን ስንመለከት ደግሞ በር -‰¼

ቀንድ -ኣም

ህዝብ -ኣዊ (8ኛ ገጽ 23) እነዚህ መልመጃዎች ምሳሌው ላይ ከተጠቀሰው ማጣመር ጋር አይመሳሰሉም፡፡ ምክንያቱም **በር ብሎ-‰¼** ሲጨመርበት ያለምንም ችግር

በረኛ ሊባል ይችላል። **ትክክለኛ** የሚለው ግን ኛ ሲነሳ ቀሪው **ትክክለ** ይሆናል። ይህ ደግሞ ከሌሎች ጋር አብሮ አይሄድም ስለዚህ ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ተገቢ አይደለም።(8ኛ ገጽ 161) በመርሀ-ትምሀርቱ አዳዲስ ቃላትን ለማንበብ የምዕላድ ትርጉም ዕውቀት (ቃል መስራች እና የእርባታ ምእላዶችን) ይጠቀማሉ ይላል፤ ነገር ግን በመማሪያ መጸሀፉ ላይ ስለዚህ ነገር የተሰጠ ማብራሪያ የለም።

ምሳሌ፡- የሚከተሉትን ቃላት በመጀመሪያ በመነጣጠል ጽፋችሁ አንብቡና መድረሻ ቅጥያዎችን አውጥታችሁ ጻፉ።

(8ኛመማሪያ መጽሀፍ ገጽ 168)

| | የተጣመሩት ቃላት | ነጣጥለው በመጻፍ ማንበብ | መድረሻ ቅጥያዎችን ብቻ መጻፍ |
|---|---|---|---|
| ሀ | ይቀርብሀል | ይ-ቀርብ-ሀ-ል | -ል |
| ለ | ይፈልግልሻል | ይ-ፈልግ-ል-ሽ-ኣል | -ኣል |
| ሐ | ይመክሩናል | ይ-መክሩ-ን-ኣል | -ኣል |
| መ | ይፈልጋል | ይ-ፈልግ-ኣል | -ኣል |

ከላይ ከቀረቡት መልመጃዎች አንዱን ወስደን ብንመለከት ይፈልገኛል የሚለውን ነጣጥለን ብንጽፍ ይ-ት-ፈለግ-ኣል የሚሉ ተዋቃሪዎችን የያዘ ተገብሯዊ የትንቢት ግስ ነው በዚህ ግስ ውስጥ የተገብሮ ምዕላዷ /ት/ በአካል አትታይም እንዲሁም ሌሎችን ከሀ-ሐ ያሉትም ቅጥቸው በግልጽ የማይታዩ ናቸው። ይህን ደግሞ ተማሪዎቹ ከምሳሌም ሆነ ከቀደመ ትምህርታቸው አላገኙትም ስለዚህ እነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የእውቀት ዳራ ግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም። በመሆኑም የተጠቀሱት መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ በላይ ከባድ ናቸው።

(8ኛ ገጽ 61) **ምኞታቸውን** የሚለው ቃል ተነጣጥሎ ሲጻፍ **ምኞት-ኣቸው-ን** ተብሎ ተጽፏል ነገር ግን መሆን የነበረበት **ምኝ-ኦት-ኣቸው-ን** ነው ነገር ግን እንደዚህ ነጣጥሎ ለመጻፍ በነሱ የክፍል ደረጃ ተገቢነት የለውም ምክንያቱም **ምኝ** ብቻውን የሚሰጠው ትርጉም አይኖርም **ምኞት** ብሎ መጻፍም ትክክል አይደለም ስለዚህ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ በላይ የሆነ ቃል አምጥቶ ተማሪውን ከማወዛገብ ሌሎች ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቃላት ቢካተቱ የተሻለ ነበር። በአጠቃላይ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች አብዛኞቹ ይዘቶች ተገቢነት ያላቸውና የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥኑ ሲሆኑ ጥቂት ይዘቶች

ግን ከተማሪው የመገንዘብ አቅም በላይ በመሆናቸው ወደ ቀጣዩ ክፍል ሊሸጋገሩ ይገባል ይህ ካልሆነ ግን ተማሪዎቹን ስለሚያስጨንቃቸው ትምህርቱን ሊጠሉት ይችላሉ

## 4.2.4. የሰዋስው ትምህርት ከተመጣጣኝነት አንጻር

Harmer (1987፡18) "የትምህርት ይዘቶቹ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተመጣጥነው ሊቀርቡ ይገባል፤ ያ ማለት ግን ሁሉም በእኩል ደረጃ ይቅረቡ ማለት አይደለም፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መጻሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዓይነትም ሆነ በመጠን ሚዛናቸውን ጠብቀውና ተመጣጥነው ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ማለትም በተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት በመስጠት ሌላውን የሰዋስው ይዘት መዘንጋት አይገባም፡፡ ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ ንኡሳን ይዘቶች ከተመጣጣኝነት አንፃር ምን እንደሚመስሉ በሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.7፡- 7ኛእናየ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት፣ የመምህሩ መምሪያና መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱ ንኡሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተመጣጣኝነት አንጻር**

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተካተቱበት | 7ኛክፍል መርሀትምህርት | | የ7ኛክፍል የመማሪያ መጻህፍት | | የ7ኛክፍል የመምህሩ መምሪያ | | 8ኛክፍል መርሀትምህርት | | የ8ኛክፍል የመማሪያ መጻህፍት | | የ8ኛክፍል የመምህሩ መምሪያ | | ጠ/ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነ ድምጽ | 1 | 2.6 | 1 | 1.4 | 1 | 1.5 | 1 | 3.6 | 1 | 1.4 | 1 | 1.7 | 6 | 1.8 |
| ስነ ምዕላድ | 18 | 47.4 | 28 | 38.4 | 22 | 34.4 | 9 | 32.1 | 26 | 36.6 | 20 | 33.3 | 123 | 36.8 |
| ስነ አገባብ | 13 | 34.2 | 24 | 32.8 | 21 | 32.9 | 13 | 46.5 | 20 | 28.2 | 21 | 35 | 112 | 33.5 |
| ስነ ፍቺ | 6 | 15.8 | 20 | 27.4 | 20 | 31.2 | 5 | 17.8 | 24 | 33.8 | 18 | 30 | 93 | 27.9 |
| ጠቅላላ ድምር | 38 | 100 | 73 | 100 | 64 | 100 | 28 | 100 | 71 | 100 | 60 | 100 | 334 | 100 |

በ7ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት፣ በመማሪያ መጽሐፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከስነድምጽ እስከ ስነፍቺ ያሉት የሰዋስው ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው አንዱ ይዘት ከሌላው ይዘት የመጠን መለያየት ይታይባቸዋል፡፡ እንዲሁም በአንድ ንኡስ ይዘት ውስጥም የስርጭት መለያየት ይታይባቸዋል፡፡ በመማሪያ መጽሀፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ አብዛኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 38.4% እና 34.4% ናቸው፡፡ እንዲሁም ስነአገባብ 32.8% እና 32.9%፣ ስነፍቺ ደግሞ 27.4% እና 31.2% ድምጽ1፣1.4% እና 1.5% ሆነው ቀርበዋል፡፡ በ7ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥም እንደ መማሪያ መጻህፉቱ እና መምህሩ መምሪያ ከፍተኛውን ቦታ የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 47.4% ይደርሳል፡፡ ሌሎች ስነአገባብ 34.2% ስነፍቺ 15.8% እንዲሁም ስነድምጽ 2.6% በደረጃ ከትልቁ ወደ ትንሹ ተቀምጠዋል፡፡ በ8ኛ ክፍል በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ከፍኛውን ድርሻ የያዘው ስነ አገባብ 35% ሲሆን በመማሪያ መጽሀፉ ደግሞ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ስነምዕላድ 36.6% ነው፡፡ ሌሎች ስነፍቺ በመምህሩ መምሪያ እና በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ 30% እና 33.8% ሲሆኑ ስነድምጽ ደግሞ በሁለቱም 1.5% ሆነው ተካተዋል፡፡ በአጠቃላይ በተተነተኑት ሁሉም ሰነዶች ውስጥ የቀሩቡት የሰዋስው ይዘቶች ከሞላጎደል ተመጣጣኝነት ያላቸው ቢሆንም ለስነድምጽ የተሰጠው መጠን ግን በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ለስነምዕላድ ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በክለሳ ድርሳን እንደተገለጸው የሰዋስው ይዘቶች ከሁሉም የቋንቋ የዕውቀት ክፍሎች ተመጥነው እንዳስፈላጊነታቸው መካተት ይኖርባቸዋል፤ ለተማሪዎቹ በቂ እውቀት ለማስጨበጥና የተሟላ የተግባቦት ችሎታ እንዲኖራቸው በተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶቹ ተመጥነው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

## 4.3. መማሪያ መጻህፍቱ፣ በመምህሩመምሪያ እና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1.ተከታታይነት

በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተገለፀው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዚያው የክፍል ደረጃ በተለያዩ ምዕራፎች ወይም በሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ እየተደጋገመ መምጣት ማለት ነው ድግግሞሹም ተማሪዎች ቀደም ሲል የተማሩትን የሰዋስው ይዘቶች በሚገባ እንዲገነዘቡ ለማድረግና በቂ እውቀት አግኝተው ወደ ቀጣይ ክፍል መሻገር እንዲችሉ የሚያግዝና ቀድሞ የተማሩትን ትምህርት የሚያጠናክር መሆን አለበት ይህም ተማሪው ለትምህርትነት የቀረበውን ይዘት ለማስረጽ እድል

ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት ሰነዶችው ውስጥ ምን ያህል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን ተደጋግመው እንደቀረቡ ቀጥሎ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማየት እንሞክር፡፡

**ሠንጠረዥ 4.8 ፡- በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከተከታታይነት አንጻር**

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽ መጠን በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ስነ ድምጽ | የድምጽ መጥበቅና መላላት | 116 | 1 | 1.4 |
| ስነ ምዕላድ | | | 28 | 38.4 |
| | ቃላትን መነጠልና ማጣመር | 1፣15፣21፣40፣56፣63፣87፣103፣109፣128፣131፣134፣148፣156፣173፣199.፣208 | 17 | 23.3 |
| | መስተዋድድ | 27 | 1 | 1.4 |
| | ተውሳከግስ | 70፣85፣197፣206፣ | 4 | 5.5 |
| | መደብ | 76፣85፣206 | 3 | 4.1 |
| | ተውላጠስም | 85 | 1 | 1.4 |
| | የቃል ክፍሎችን መመደብ | 160 | 1 | 1.4 |
| | ቃላትን ማርባትና መመስረት | 204 | 1 | 1.4 |
| ስነአገባብ | | | 24 | 32.8 |
| | ድርብዓረፍተነገሮችንመነጠልና መመስረት | 13፣20፣133 | 3 | 4.1 |
| | አያያዦችን መጠቀም | 32፣39፣99፣ | 3 | 4.1 |
| | ጠቋሚመስተአምር | 48፣54፣62፣164፣179 | 5 | 6.8 |
| | አውንታዊናአሉታዊ ዓረፍተነገር | 94፣216 | 2 | 2.7 |
| | መጠይቃዊ ቃላትና አረፍተነገሮች | 102፣108፣224 | 3 | 4.1 |
| | ውስብስብዓረፍተነገር መመስረት | 119፣154 | 2 | 2.7 |
| | ጥገኛዓረፍተነገር መመስረት | 141፣147 | 2 | 2.7 |
| | በዓ.ነገር ውስጥ የቃላት አጠቃቀም | 145፣223 | 2 | 2.7 |
| | ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ | 172 | 1 | 1.4 |
| | ጊዜ | 188፣206 | 1 | 1.4 |
| ስነፍቺ | | | 20 | 27.4 |
| | የቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት | 5፣24፣30፣37፣67፣91፣106፣126፣168፣213 | 10 | 13.7 |
| | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠት | 11፣18፣45፣74፣82 | 5 | 6.8 |
| | የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | 52፣59፣177 | 3 | 4.1 |
| | የቃላትና የሀረጋት ቀጥተኛ /መዝገበ ቃላዊ ፍቺ | 137፣ | 1 | 1.4 |
| | በጥንድ ቃላት መካከል ያለ የፍቺ ልዩነት | 185 | 1 | 1.4 |
| | | | 73 | 100 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በተተኳሪው መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በስነምዕላድ ውሰጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቃላትን ማጣመርና መነጣጠል 17(23.3) ጊዜ ሲሆን ሌሎች መደብ 3(4.1) ጊዜ፣ ተውሳከግስ 4(5.5) ጊዜ ሲደጋገሙ የተቀሩት ይዘቶች አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ተካተዋል፡፡ በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ ጠቋሚ መስተአምር 5(6.8) ጊዜ መጠይቃዊ አረፍተነገሮች እና አያያዦች ሶስት ሶስት ጊዜ ሲደጋገሙ አውንታዊ፣ እና አሉታዊ ዓረፍተነገር ሁለት ሁለት ጊዜ እንዲሁም ስሞችን እንደ መሙያ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡ በስነ-ፍች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ የሚለው ሲሆን የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ አምስት ጊዜ፣ የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ ሶስት ጊዜ የተደገመ ሲሆን የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ እና በጥንድ ቃላት መካከል ያለ የፍቺ ልዩነት የሚሉት አንድ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡ በመሆኑም በ7ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሀፍ ውስጥ አንዳንድ ይዘቶች በከፍተኛ ደረጃ ሲደገሙ አንዳንድ ይዘቶች አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡበት ሁኔታ አለ፡፡

ሠንጠረዥ 4.9 ፡- በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ ከተከታታይነት አንጻር

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽ መጠን<br>በቁጥር | <br>በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ስነድምጽ | የድምጽ መጥበቅ እና መላላት | 71 | 1 | 1.5 |
| ስነምዕላድ | | | 22 | 34.4 |
| | ቃላትን መነጠል እና ማጣመር | 11፣24፣28፣41፣51፣69፣84፣99፣116፣133 | 10 | 15.6 |
| | ጊዜ | 121፣127፣131 | 3 | 4.7 |
| | መደብ | 50፣54 | 2 | 3.1 |
| | ተውሳከ ግስ | 45፣54፣131፣135 | 3 | 4.7 |
| | መስተዋድድ | 19፣42 | 1 | 1.5 |
| | የቃል ክፍሎችን መመደብ | | 3 | 4.7 |
| ስነአገባብ | | | 21 | 32.9 |
| | ውስብስብ ዓ.ነገር መመስረት | 75፣83 | 2 | 3.1 |
| | ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ | 110 | 1 | 1.5 |
| | ሀረጋትን መመስረት | 96 | 1 | 1.5 |
| | አውንታዊናአሉታዊ ዓረፍተነገር | 60፣68፣139 | 3 | 4.7 |
| | መጠይቃዊ ቃላትና አረፍተነገሮች | 64፣68፣143 | 3 | 4.7 |
| | ጥገኛዓረፍተነገር መመስረት | 90፣94 | 2 | 3.1 |
| | አያያዦችን መጠቀም | 23፣62 | 2 | 3.1 |
| | ተውላጠ ስም | 54 | 1 | 1.5 |
| | ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ | 101 | 1 | 1.5 |
| | ጠቋሚመስተአምር | 32፣35፣46፣105፣114 | 5 | 7.8 |
| ስነፍቺ | | | 20 | 31.2 |
| | በጥንድ ቃላት መካከል ያለ የፍቺ ልዩነት | 118 | 1 | 1.5 |
| | የቃላት አውዳዊ ፍቺመስጠት | 16፣21፣43፣66፣77፣81፣107፣136 | 12 | 18.7 |
| | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠት | 29፣48፣52፣86 | 4 | 6.2 |
| | የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | 33፣112 | 2 | 3.1 |
| | የቃላትና የሀረጋት ቀጥተኛፍቺ | 33 | 1 | 1.5 |
| | | | 64 | 100 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በ7ኛ ክፍል መምህሩ መማሪያ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በስነምዕላድ ውሰጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቃላትን ማጣመርና መነጣጠል አስር ጊዜ ሲሆን፣ ተውሳከግስ አራት ጊዜ መደብ እና መስተዋድድ ሁለት ሁለት ጊዜ፣ ሲደጋገሙ የቃል ክፍሎችን መመደብ አንድ ጊዜ ብቻ ተካተዋል፡፡

በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ ጠቋሚ መስተአምር አምስት ጊዜ አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር እና መጠይቃዊ ቃላትና አረፍተ-ነገሮች ሶስት ሶስት ጊዜ ሲደጋገሙ ጥገኛ ዓረፍተ-ነገሮችን መመስረት እና አያያዦችን መጠቀም ሁለት ሁለት ጊዜ እንዲሁም ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ እና ተውላጠ ስም አንድ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡ በስነፍቺ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ አስራ ሁለት ጊዜ ተደጋገመ ሲሆን የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ አራት ጊዜ፣ የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ ሁለት ጊዜ የተደገመ ሲሆን የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ደግሞ አንድ ጊዜ ተካቷል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ በመነሳትና በ7ኛ ክፍል መምህሩ መማሪያ ውስጥ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አንዱ ካንዱ የመበላለጥና በተጠጋጋ መጠን ካለመደገሙ ተነሳ የተከታታይነት ችግር እንዳለው ለማስተዋል ተችሏል፡፡

### ሠንጠረዥ 4.10፡- በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት ከተከታታይነት አንጻር

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽ መጠን በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ስነድምጽ | | 161 | 1 | 2.6 |
| ስነምዕላድ | | | 18 | 47.4 |
| | ውስብስብ ምዕላድ ያላቸውን ቃላት መፈደል | 152፣161፣162፣ | 3 | 7.9 |
| | ቃላትን መመስረት | 152፣152፣152፣161፣ | 4 | 10.5 |
| | ነጻና ጥገኛ ምዕላድ | 152፣161 | 2 | 5.26 |
| | ቅጥያዎች | 154፣155፣164 | 3 | 7.9 |
| | እንደመሙያ ሚያገለግሉ ስሞች | 155፣165 | 2 | 5.26 |
| | ቃል መስራችና የእርባታ ምዕላድ | 152፣161 | 2 | 5.26 |
| | ተውሳከግሶች | 155፣164፣ | 2 | 5.26 |
| ስነአገባብ | | | 13 | 34.2 |
| | አውንታዊና አሉታዊ መጠይቆች | 154፣164፣ | 2 | 5.26 |
| | ድርብ አረፍተነገሮች | 155፣165 | 2 | 5.26 |
| | መጠይቃዊ አረፍተነገሮች | 155፣165፣ | 2 | 5.26 |
| | እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች | 154.155.165 | 3 | 7.9 |
| | ጠቋሚ መስተአምር | 154 | 1 | 2.6 |
| | ዓረፍተነገሮችን ወደ ጥገኛ ሀረግ መለወጥ | 161፣164 | 2 | 5.26 |
| | ቃላትን ማርባት | | 1 | 2.6 |
| ስነፍቺ | | | 6 | 15.8 |
| | ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ይለያሉ | 167፣168 | 2 | 5.26 |
| | ቃላትን ከአውዱ መገመት | 166፣156፣ | 2 | 5.26 |
| | ለቃላትና ለሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት | 166፣165፣ | 2 | 5.26 |
| | | | 38 | 100 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በ7ኛ ክፍል መርሀትምህርት ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ ስነምዕላድ ሲሆን ከስነምዕላድ ውስጥ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቃላትን መመስረት አራት ጊዜ ሲሆን ውስብስብ ምዕላድ ያላቸውን ቃላት መፈደል እና ቅጥያዎች ሦስት ሦስት ጊዜ፣ ነጻና ጥገኛ ምዕላድ ቃል መስራትና የእርባታ ምዕላድ ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው ተደራጅተዋል፡፡ በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች ሶስት ጊዜ፣ አውንታዊና አሉታዊ አረፍተነገሮች፣ ጥገኛ ዓረፍተ-ነገሮችን መመስረት፣ መጠይቃዊ አረፍተነገሮች እና ድርብ አረፍተነገሮች ሁለት ሁለት ጊዜ ሲደጋገሙ ጠቋሚ መስተአምር እና ቃላትን ማርባት አንድ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡ በስነፍቺ ውስጥ ደግሞ የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ፣ የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ፣ የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡

## ሠንጠረዥ 4.11 ፡- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከተከታታይነት አንጻር

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝርየሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽ መጠን በቁጥርበመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|
| ስነድምጽ | | 189 | 1 | 1.4 |
| ስነምዕላድ | | | 26 | 36.6 |
| | ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር | 1፣24፣44፣61፣67፣85፣110፣136፣159፣168፣185፣238፣ | 12 | 16.9 |
| | ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተአምር | 30፣36፣42፣152፣158፣167፣ | 6 | 8.4 |
| | የቃላት ቅጥያዎችን አጣምሮ መጻፍ | 35፣51 | 2 | 2.8 |
| | ቃላትን እያረቡ መጻፍ | 58፣ | 1 | 1.4 |
| | ጊዜ አመልካች | 60፣66፣176፣191፣ | 4 | 5.6 |
| | እንደመሙያየሚያገለግሉ ስሞች | 84 | 1 | 1.4 |
| ስነአገባብ | | | 20 | 28.2 |
| | አውንታዊ አረፍተነገሮችን ወደ አሉታዊ መለወጥ | 10፣23፣127፣143፣ | 4 | 5.6 |
| | መጠቃዊዓረፍተነገሮችን መመስረት | 17፣109፣134፣ | 3 | 4.2 |
| | ዓረፍተነገሮችን ወደ ጥገኛሀረግ መለወጥ | 76፣91፣229፣247 | 4 | 5.6 |
| | ነጠላ አረፍተነገሮችን በማቀናጀት ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት | 99፣214፣ | 2 | 2.8 |
| | የቃላት አጠቃቀም (ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀም ሀረጋትን ማዋቀር) | 173፣188 | 2 | 2.8 |
| | ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመስረት | 188፣191 | 2 | 2.8 |
| | ስማዊ ሀረጎችን በመሙያነት መጠቀም | 208፣217፣247፣ | 3 | 4.2 |
| ስነፍቺ | | | 24 | 33.8 |
| | የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ | 5፣105፣113፣156፣ | 4 | 5.6 |
| | የቃላት ተቃራኒ ፍቺ | 5፣63፣113፣148፣ | 4 | 5.6 |
| | የቃላት አውዳዊ ፍቺ | 15፣21፣27፣41፣57፣73፣123፣132፣139፣164፣193፣224 | 12 | 16.9 |
| | ቃላትን መመደብና ፍቺ መስጠት | 34፣48፣ | 2 | 2.8 |
| | ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች መጻፍና በአረፍተነገር ውስጥ መጠቀም | 96፣180 | 2 | 2.8 |
| | | | 71 | 100 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በስነምዕላድ ውሰጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቃላትን ማጣመርና መነጣጠል አስራ ሁለት ጊዜ ሲሆን ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተአምር ስድስት ጊዜ አመልካች ቅጥያ አራት ጊዜ ፣የቃላት ቅጥያዎችን አጣምሮ መጻፍ ሁለት ጊዜ፣ ቃላትን እያረቡ መጻፍና እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች አንድ አንድ ጊዜ ተከተው ቀርበዋል፡፡ በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ ጥገኛ ዓረፍተነገሮችን መመስረት እና አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር አራት ጊዜ መጠይቃዊ አረፍተነገሮች እና ስማዊ ሀረጎችን በመሙያነት ሶስት ጊዜ ሲደጋገሙ የቃላት አጠቃቀም፣ ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመስረት እና ድረብ ዓረፍተነገር መመስረት ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ በስነፍቺ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ አራት ጊዜ ተደጋገመ ሲሆን የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ እና የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ አራት ጊዜ የተደገመ ሲሆንቃላትን መመደብና ፍቺ መስጠት እና ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች መጻፍና በአረፍተነገር ውስጥ መጠቀም ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ በመነሳትና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሀፍ ውስጥ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አንዱ የተቀራረበ አይደለም በተለይ በስነፍቺ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች መካከል የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ በከፍተኛ ሁኔታ ሲደጋገም ሌሎች ደግሞ በዝቅተኛ መጠን የመደገም ችግር እንዳለው ለማስተዋል ተችሏል፡፡

### ሠንጠረዥ 4.12፦ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ ከተከታታይነት አንጻር

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽመጠን በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ስነድምጽ | | | 1 | 1.7 |
| ስነምዕላድ | | | 20 | 33.3 |
| | ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር | 14፣24፣28፣44፣56፣61፣74፣95፣121፣136፣142፣162 | 12 | 20 |
| | ተውሳከ ግስ | 18፣23፣120 | 3 | 5 |
| | ጊዜ አመልካች ቅጥያዎች | 34፣38፣43፣130፣141 | 5 | 8.3 |
| ስነአገባብ | | | 21 | 35 |
| | አውንታዊ አረፍተነገሮችን ወደ አሉታዊ መለወጥ | 7፣86፣93፣99፣101 | 5 | 8.3 |
| | መጠቃዊዓረፍተነገሮችን መመስረት | 73፣93፣178 | 3 | 5 |
| | ዓረፍተነገሮችን ወደ ጥገኛሀረግ መለወጥ | 160፣171፣185 | 3 | 5 |
| | ጠቋሚ መስተአምር | 114 | 1 | 1.7 |
| | መስተጻምር | 23፣114 | 2 | 3.3 |
| | ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት | 140 | 1 | 1.7 |
| | ስማዊ ሀረጎችን በመሙያነት መጠቀም | 54፣155 | 2 | 3.3 |
| | አያያዦች | 17፣81፣178 | 3 | 5 |
| | ዓ.ነገሮችን በአይነት መመደብ | 78 | 1 | 1.7 |
| ስነፍቺ | | | 18 | 30 |
| | ቃላትን በተለያየ ቅርጽ መጻፍ | 63 | 1 | 1.7 |
| | የቃላት ተመሳሳይ እናተቃራኒ ፍቺ | 16፣40፣57፣111፣154፣158 | 6 | 10 |
| | የቃላት አውዳዊ ፍቺ | 9፣12፣15፣25፣30፣36፣46፣82፣96 | 9 | 15 |
| | ቃላትን መመደብና ፍቺ መስጠት | 21 | 1 | 1.7 |
| | የቃላት አጠቃቀም | 123 | 1 | 1.7 |
| | | | 60 | 100 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በስነምዕላድ ውሰጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቃላትን ማጣመርና መነጣጠል አስራ ሁለት ጊዜ ሲሆን ጊዜ አመልካች ቅጥያ አምስት ጊዜ እና ተውሳከግስ ሶስት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር አምስት ጊዜ ጥገኛ ዓረፍተነገሮችን መመስረት እና መጠይቃዊ አረፍተነገሮች

እና አያያዦች ሦስት ሦስት ጊዜ እና ስማዊ ሀረጎችን በመሙያነት መጠቀም እና መስተጻምር ሁለት ሁለት ጊዜ ሲደጋገሙ የቃላት አጠቃቀም ጠቋሚ መስተአምር፣ ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመስረት እና ዓረፍተነገሮችን በአይነት መመደብ አንድ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡ በስነፍቺ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቺ ሰባት ጊዜ ተደጋገመ ሲሆን የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ስድስት ጊዜ የተደገመ ሲሆን ቃላትን መመደብና ፍቺ መስጠት፣ ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች መጻፍና የቃላት አጠቃቀም ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ተካተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.13 ፡- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት ውስጥ ተከታታይነት**

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ዝርዝርየሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የመገኛ ገጾቻቸው | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነድምጽ | | 192 | 1 | 3.6 |
| ስነምዕላድ | | | 9 | 32.1 |
| | ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር | 190፣200፣ | 2 | 7.1 |
| | ቃል መስራችና የእርባታ ምዕላድ | 190፣200፣ | 2 | 7.1 |
| | ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተአምር | 193፣202 | 2 | 7.1 |
| | ቅጥያዎች | 192፣193፣202 | 3 | 10.7 |
| ስነአገባብ | | | 13 | 46.5 |
| -,- | ጥገኛሀረጎች እና እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች | 193፣203 | 2 | 7.1 |
| | አውንታዊ አረፍተነገሮችን | 192፣202 | 2 | 7.1 |
| | መጠቃዊዓረፍተነገሮችን መመስረት | 193፣203፣ | 2 | 7.1 |
| | ጊዜ አመልካች ምእላዶች | 193፣2002፣203፣ | 3 | 10.7 |
| | ድረብ ዓረፍተነገር መመስረት | 193፣203 | 2 | 7.1 |
| | ውስብስብ አረፍተነገሮች | 192፣203 | 2 | 7.1 |
| ስነፍቺ | | | 5 | 17.8 |
| | ተቃራኒ ፍቺ | 194፣፣203 | 2 | 7.1 |
| | አውዳዊ ፍቺ | 194፣200፣203፣204፣ | 3 | 10.7 |
| | | | 28 | 100 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በስነምዕላድ ውሰጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው ቅጥያዎች ሶስት ጊዜ ሲሆን ሌሎች ቃላትን ማጣመርና መነጣጠል፣ ቃል መስራችና የእርባታ ምዕላድ እና ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተአምር ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ በስነአግባብ ውስጥ ደግሞ ጊዜ አመልካች ምእላዶች ሶስት ጊዜ አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር፣ ጥገኛሀረጎች እና እንደመሙያ የሚያገለግሉ ስሞች፣ መጠይቃዊ አረፍተነገሮች፣ ውስብስብ አረፍተነገሮች፣ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት ጊዜ እና ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ በስነፍቺ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተደገመው የቃላትና የሀረጋት አውዳዊ/አገባባዊ ፍቺ ሶስት ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን የቃላትና የሀረጋት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ 2 ጊዜ ተደጋግሞ ተደራጅቷል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በእኩል ደረጃ ድግግሞሽ ይኖራቸዋል ተብሎ ባይታሰብም የይዘቶቹ የድግግሞሽ መጠን ተቀራራቢ ሊሆን ይገባል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ ካሉት የሰዋስው ይዘቶች ለምሳሌ በስነምዕላድ ውስጥ ካሉት መካከል ከፍተኛውን የድግግሞሽ መጠን  የያዘው ቃላትን መነጠልና ማጣመር ሲሆን ሌሎች ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ልዩነት ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት የሚገድብ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ይዘቶች በዝቅተኛ መጠን መደጋገም ተማሪዎቹ በዚያ ይዘት ላይ ምንም ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ከፍ ወዳለው የክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ለዚያ ይዘት አዲስ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ሲዘጋጅ የተመጣጠነ የድግግሞሽ መጠን ቢኖራቸው የተሻለ ነው፡፡

## 4.3.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት አንድ የትምህርት ይዘት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተደጋግሞ መምጣትን የሚያመለክት ሆኖ ይዘቶቹም ቀጣይነት ባለው መልኩ እርስበእርሳቸው ተሳስረው ስፋትና ጥልቀታቸውም እየጨመረ መሄድ እንዳለበት በክለሳ ድርሳን ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ  የተካተቱ ይዘቶች ሲደራጁ የድግግሞሽ ሁኔታቸው ጥልቀትና ክብደት እየጨመረ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ቀጥለን በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡትን የተለጣጣቂነት ሁኔታ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ለምሳሌ (7ኛክፍል መማሪያ መጻሀፍ በገጽ 94) ስለአውንታዊና አሉታዊ አረፍተነገሮችን ማብራሪያ በመስጠት አውንታዊና አሉታዊ የሆኑ አረፍተነገሮችን ለዩ፣ (በ8ኛ ክፍል ገጽ

10) አውንታዊ ዓረፍተነገሮችን ወደ አሉታዊ ለውጡ እንዲሁም አምስት አውንታዊና አሉታዊ አረፍተ-ነገሮችን ጻፉ፡፡

7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሀፍና የመምህሩ መምሪያ ስለተውሳከ ግስ በቀረበ ይዘት መጀመሪያ ስለተውሳከግስ ምንነት ያብራራና ቀጥሎ የጊዜና የቦታ ተውሳከ ግስ ከዚያም በ8ኛ ክፍል ደግሞ ተውሳከግሶችን ለዩ፣ ተውሳከ-ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ ይላል፡፡

በመርሀትምህርቶቹም ላይ በ7ኛክፍል አውንታዊና አሉታዊ የሆኑ አረፍተነገሮችን መለየት በ8ኛክፍል ላይ ደግሞ አውንታዊና አሉታዊ የሆኑ አረፍተነገሮችን መጻፍ ይላል፡፡ ስለዚህ የሰዋስው ይዘቶቹ ሲለጣጠቁ ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ ጭምር መሄዱን ከነዚህ ለአብነት ያህል ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የቅጥያዎችን ይዘት በተመለከተ በ7ኛ ክፍል ላይ ቅጥያዎችን መለየት፣ በ8ኛ ክፍል ላይ ደግሞ በአብዛኛው ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን በመለየት እንዲሁም ቃል መስራችና የእርባታ ቅጥያዎችን በብዛት ደግሞ የእርባታ ቅጥያዎችን ለምሳሌ የዘርፍ የቁጥር፣ የመደብ አመልካቾችን ለዩ የሚሉ መልመጃዎች ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የተደራጁ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ ምንም እንኳ መጻሕፍቱ የሚጋሯቸው በርካታ ይዘቶች ቢኖሯቸውም የተወሰኑት ይዘቶች ደግሞ ከ7ኛ ክፍል ወደ 8ኛ ክፍል ብዙም ለውጥ ሳያሳዩ ሲቀርቡና ከክፍል ወደ ክፍል ሳይሸጋገሩ ይታያል፡፡ ለምሳሌ መስተዋድድ፣ በጥንድ ቃላት መካከል የፍቺ ልዩነት፣ ተውላጠ ስም የሚሉት ይዘቶች በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ላይ እና በመምህሩ መምሪያ ላይ ብቻ አንድ አንድ ግዜ ብቻ የቀረቡ ሲሆኑ፤ የቃል ክፍሎችን መመደብ፣ ቃላታን ማርባትና መመስርት፣ የሚሉት ይዘቶች ደግሞ ከ7ኛ ክፍል ወደ 8ኛክፍል ሲሸጋገሩ ምንም ለውጥ ያላሳዩ ናቸው፡፡ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጸሀፍ ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች መጻፍና በአረፍተነገር ውስጥ መጠቀም፣ የማሰሪያ አንቀጽ ሙያ መለየት፣ ቃላትና ሀረጋትን በማጣመር ሀረጋትን ማዋቀር የሚሉት እንዲሁም በ7ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት ውስጥ ቃል መስራችና የእርባታ ምእላድ፣ እስርና ነጻ መዕላዶች የሚሉት ይዘቶች ምንም ተከታታይነት የሌላቸው በ8ኛክፍል መማሪያ መጻሀፍ ላይ፣ በመምህሩ መምሪያ ላይ እና በመርሀትምህርቱ ላይ ብቻ የቀመጡ ይዘቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች የተለጣጠቁበት መንገድ ከጥቂት ይዘቶች በስተቀር በአብዛኛው በክለሳ ድርሳን የተነሳውን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ የማይገድብ እና ከአንዱ ክፍል ደረጃ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ቀዳሚው ለተከታዩ መሰረት በሚሆን መልኩ የተዋቀሩ በመሆናቸው

ተማሪው ቀድሞ ያልተገነዘበውን ጽንሰ ሀሳብ እንዲገነዘብና ቀጣዩን ትምህርት በቀላሉ እንዲረዳው እድል የሚሰጡ ናቸው፡፡

### 4.3.3. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

በተተኳሪዎቹ መጻህፍት የቋንቋው ሰዋስዋዊ ህግ በማብራሪያ፣ በገለጻና ምሳሌዎች ታግዞ ከቀረበ በኋላ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ አካሄዶች ታይተዋል፡፡ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍ እና በመምህሩ መምሪያ ማስታወሻ እና ምሳሌ በመስጠት የቀረቡ መልመጃዎች (በ7ኛ ክፍል ገጽ1) ቃላትን መነጠልና ማጣመር፣ (በገጽ 8) ስለአያያዥ ቃላት፣ በ(ገጽ 13) ድርብ ዓረፍተነገሮችን ስለመነጠል ምሳሌ በመስጠት፣ በገጽ27 ስለመስተዋድድ፣ (በገጽ 48) ስለጠቋሚ መስተአምር፣ (በገጽ 54) ስለጠቋሚ መስተአምር እና የመሆንግስ፣ (ገጽ76) ስለመደብ፣ (በገጽ 94) ስለአውንታዊና አሉታዊ አረፍተነገሮች፣ (ገጽ 102)፣ ስለመጠይቃዊ ቃላት እና አረፍተነገሮች (በገጽ 141) ስለጥገኛ አረፍተነገሮች፣(ገጽ 188) ስለጊዜ እንዲሁም በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ(በገጽ 23) ስለ መደብ (ገጽ 76) ስለጥገኛ ሀረግ፣ (ገጽ 99) ስለ ወደረኛ መስተጻምር በ7ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ውስጥ (በገጽ 6 )ስለ አያያዦች፣(ገጽ 19) ስለ መስተዋድድ፣ (ገጽ 23) ስለ አያያዦች፣ (ገጽ 45) ስለተውሳከ ግስ እንዲሁም በ8ኛ ክፍል መምህሩ መምሪያ ላይ (ገጽ 7)ስለ አሉታዊና አውንታዊ ዓረፍተነገሮች፣(ገጽ 13) ዓረፍተነገሮችን በአይነት መመደብ፣ (ገጽ 67) ነጠላ አረፍተነገሮችን ስለ ማቀናጀት የተሰጡት ማብራሪያዎች እና መልመጃዎች ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አካሄድን የተከተሉ እንደሆነ ማሳያ ናቸው፡፡

ለምሳሌ 7ኛ ክፍል ገጽ 27ላይ

## መስተዋድድ

## ማስታወሻ፡-

መስተዋድድ አንድን አረፍተነገር ግሱ እንዳያስር ከሌላ አረፍተነገር ጋር እንዲጠጋ የሚያደርግ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ስለ-እንደ-ከ-ለ-ወደ እና መሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በጥንድ የቀረቡትን አረፍተነገሮች በመስተዋድድ በማያያዝ ውስብስብ አረፍተነገሮች መስርቱ

ምሳሌ፡-አህመድ ቶሎ መጣ፡፡

አህመድ ደብተሩን አገኘ፡፡ } አህመድ ቶሎ ስለመጣ ደብተሩን አገኘ፡፡

ከላይ በአስረጂነት የቀረበውን ምሳሌ ስንመለከት አስቀድመው ስለ መስተዋድድ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ምሳሌ ሰጠ፤ በማስከተልም ተማሪዎች የሚለማመዷቸውን መልመጃዎች አቀረበ፡፡ ተማሪዎቹም በተሰጣቸው ገለጻ እና በቀረበላቸው ምሳሌ መሠረት የተሰጣቸውን መልመጃ ይሰራሉ፡፡

## 4.3.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

በሌላ በኩል ደግሞ ለቀረበው ይዘት ምሳሌዎችን በማቅረብና ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት በራሳቸው ወደ ሚፈለገው የቋንቋ ህግ ላይ እንዲደርሱ የሚያደርግ አካሄድ በተተኳሪዎቹ መጻህፍትና መርሀትምህርቶች ውስጥ ይታያል፡፡ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሀፍ ውስጥ በገጽ20፣ 30፣ 39፣ 62፣ 85፣ 91 ፣99 ፣116 ፣ 127 ፣133 ፣145፣147፣154፣164፣172፣179፣197፣206 እና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሀፍ ውስጥ በገጽ10፣ 17፣23፣30 ፣31፣36፣42፣ 51፣58፣60፣ 66፣84፣91፣ 109፣127፣ 134፣143፣152፣158፣167፣176፣188፣191፣208፣214፣217፣247፤ በ8ኛ ክፍል መምህሩ መምሪያ ላይ ገጽ 68፣83፣94፣114፤በ7ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ውስጥ በገጽ13፣27፣32፣40.54፣68 ላይ ያሉት መልመጃዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህ አደረጃጀትም በተለይ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት እና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ተዘውትሮ የሚታይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መጻህፍቱ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን በሰፊው እንደተጠቀሙ የሚሳይ ነው፡፡

8ኛ ክፍል ገጽ17

## መጠይቃዊ አረፍተነገር

ሦስት ሀተታዊ አረፍተነገሮችን በመጻፍ በምሳሌው መሰረት የተለያዩ መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ፡፡

**ምሳሌ፡-**ዘነበች ትናንትና ከገጠር ከእህቷ ጋር በፈረስ ለስራ ፈጥና መጣች፡፡

ሀ. ማን መጣች?

ለ. ዘነበች መቼ መጣች?

ሐ. ዘነበች እንዴት መጣች?

መ. ዘነበች በምን መጣች?

ሠ. ዘነበች ለምን መጣች?

ረ. ዘነበች ከየት መጣች?

ከዚህ በላይ በአስረጂነት የቀረበውን ስንመለከት ተማሪዎቹ ከላይ የቀረበውን ምሳሌ ብቻ በመመልከት ከሀተታዊ አረፍተነገሮች መጠይቃዊ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡ መማሪያ መጻህፍቱ እና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዚህ ሁኔታ የተደራጁ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የሁሉቱም ክፍል መማሪያ መጻህፍት እና የመምህሩ መምሪያ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቶችን ተግባራዊ ያደረጉ ቢሆንም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት በአመዛኙ በሁሉም ሰነዶች የተዘወተረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ በክለሳ ድርሳን ከተነሳው ሀሳብ አንጻር አንዱን ስልት ብቻ አብዝቶ መጠቀም ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለቱም አደረጃጀቶች የየራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ሊኖራቸው ስለሚችል ሁለቱንም አጣጥሞና አመጣጥኖ መጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡

## 4.4. የውጤት ማብራሪያ

ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ እና አደረጃጀት ተጣጥሞሽ በሰነድ ፍተሻ አማካይነት ተፈትሾ ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አንጻር የተገኘው ውጤት ከምሁራን ሃሳብና ከሌሎች ቀደምት ጥናቶች አንጻር እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

Rechards (1987) ስለ መማሪያ መጽሀፍትና ስለ መርሀ ትምህርት ግኙኝነት ሲገልጽ መማሪያ መጻህፍት በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በመመስረት ተዘጋጅቶ በመምህሩና በተማሪዎች አማካይነት በተግባር ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም መማሪያ መጻህፍት የሚገመገሙት በመርሀ ትምህርቱ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡ በተተኳሪዎቹ መርሃ ትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱት የስዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ በመማሪያ መጽሐፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በመማሪያ መጻህፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስነምዕላድ 35.5%፣ ስነአገባብ 32.5%፣ ስነፍቺ 30% እና ስነድምጽ 2% ሲሆን በመርሀ-ትምህረቶቹ ውስጥ ከቀረቡት ደግሞ ስነምዕላድ 41%፣ ስነአገባብ 39.3%፣ ስነፍቺ 16.7% እና ስነድምጽ 3% ናቸው፡፡ ስለዚህ በሁሉም በመምህሩ መምሪያ፣ በመማሪያ መጻህፍቱና በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ከፍተኛውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን ዝቅተኛውን ቁጥር የያዘው ደግሞ ስነድምጽ ነው፡፡ እንዲሁም ሌሎች ስነአገባብና ስነፍቺም ተቀራራቢ ይዘት አላቸው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ተመጣጣኝ ውክልና ያላቸው በመሆኑ

በመጻህፍቱና በመርሀ-ትምህርቶቹ መካከል ጥብቅ የሆነ ተጣጥሞሽ እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎች አኳያ በሰነድ ፍተሻ ተፈትሾ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

**ከግልጽነት አንጻር፡-** በአብዛኛው ቃላትን መነጣጠልና ማጣመር ላይ የመመሪያም ሆነ የምሳሌም ግልጽነት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ቃላቱ ሲነጣጠሉ በነጻና ጥገኛ ምዕላዶች ይሁን በድምጸልሳን ይሁን በየትኛው መንገድ እንደሚነጣጠሉ የተቀመጠ ግልጽ ትእዛዝ የለም፡፡ እንዲሁም በአንድ ትእዛዝ ውስጥ ሁለት አይነት አሠራሮች በተደጋጋሚ ይታያሉ፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎቹ ላይ የእውቀት ክፍተት እንዲፈጠርና በትምህርቱ ላይ እርገጠኛ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

**ከትክክለኛነት አንጻር፡-** በአጠቃላይ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ውስጥ ጥቂት ይዘቶች የትክክለኛነት ችግር ታይቶባቸዋል፡፡ በክለሳ ድርሳን እንደተገለጸው ተማሪዎች እንዲያውቋቸው የሚፈለገውን የሰዋስው ዕውቀት የተዛባ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ትምህርቱ ከእውነተኛው አለም ጋር የማይገናኝና ተጨባጭነት የሌለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

**ከተገቢነት አንጻር፡-** በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች አብዛኞቹ ይዘቶች ተገቢነት ያላቸውና የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥኑ ሲሆኑ ጥቂት ይዘቶች ግን ከተማሪው የመገንዘብ አቅም በላይ በመሆናቸው ወደ ቀጣዩ ክፍል ሊሸጋገሩ ይገባል፡፡

**ከመመጣጠን አንጻር፡-** በተተነተኑት ሁሉም ሰነዶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ከሞላጎደል ተመጣጣኝነት ያላቸው ቢሆንም ለስነድምጽ የተሰጠው መጠን ግን በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ለስነምዕላድ ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ ከተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በክለሳ ድርሳን እንደተገለጸው የሰዋስው ይዘቶች ለተማሪዎቹ በቂ እውቀት ለማስጨበጥና የተሟላ የተግባቦት ችሎታ እንዲኖራቸው በተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶቹ ተመጥነው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን በተመለ

ከተ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተከታታይነትን በተመለከተ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች በእኩል ደረጃ ድግግሞሽ ይኖራቸዋል ተብሎ ባይታሰብም የይዘቶቹ የድግግሞሽ መጠን ተቀራራቢ ሊሆን ይገባል፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ ካሉት የሰዋስው ይዘቶች ለምሳሌ በስነምላድ ውስጥ ካሉት መካከል ከፍተኛውን የድግግሞሽ መጠን የያዘው ቃላትን መነጠልና ማጣመር ሲሆን ሌሎች ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ልዩነት ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት የሚገድብ ነው፡፡ ምክንያቱም የአንዳንድ ይዘቶች በዝቅተኛ መጠን መደገም ወይም ሳይደገም መቅረት ተማሪዎቹ በዚያ ይዘት ላይ ምንም አይነት ግንዛቤ  እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ከፍ ወዳለው የክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ለዚያ ይዘት አዲስ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት በተተኳሪዎቹ ሰነዶች የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ሲዘጋጅ የተመጣጠነ የድግግሞሽ መጠን ቢኖራቸው የተሻለ ነው፡፡

**ከተለጣጣቂነት አንጻር፡-** በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች የተለጣጠቁበት መንገድ ከጥቂት ይዘቶች በስተቀር በአብዛኛው በክለሳ ድርሳን የተነሳውን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ የማይገድብ እና ከአንዱ ክፍል ደረጃ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ቀዳሚው ለተከታዩ መሰረት በሚሆን መልኩ የተዋቀሩ በመሆናቸው ተማሪው ቀድሞ ያልተገነዘበውን ጽንሰ ሀሳብ እንዲገነዘብና ቀጣዩን ትምህርት  በቀላሉ እንዲረዳው እድል የሚሰጡ ናቸው፡፡

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን በተመለከተ የሁሉቱም ክፍል መማሪያ መጻህፍት እና የመምህሩ መምሪያ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቶችን ተግባራዊ ያደረጉ ቢሆንም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት በአመዛኙ በሁሉም ሰነዶች የተዘወተረ መሆኑን ከተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ በክለሳ ድርሳን ከተነሳው ሀሳብ አንጻር አንዱን ስልት ብቻ አብዝቶ መጠቀም ተገቢ በለመሆኑ ሁለቱንም አደረጃጀቶች አመጣጥኖ መጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ከመርሀ-ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡

በተተኳሪዎቹ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸው ናቸው? በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ለክፍል ደረጃው በተዘጋጁት መርሃ-ትምህርቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው? በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መርሆዎችን የተከተሉ ናቸው? በመማሪያ መጻሕፍቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመማሪያ መጻሕፍት አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር እንዴት ተደራጁ? የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍቱና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች ተጣጥሞሽ ለመፈተሽ በተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን በሰንጠረዥ፣ በቁጥር እና በመቶኛ ተሰልተው በገላጭ ስልት ተብራርተዋል ፡፡

በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻህፍቱና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ሲታይ በመርሀ-ትምህርቶቹ የተካተቱት አጠቃላይ የሰዋስው ይዘቶች 66 ሲሆኑ ስነምዕላድ 27 (41%) ስነአገባብ 26(39.3%) ስነፍቺ 11(16.7%) እንዲሁም ስነድምጽ 2(3%) ናቸው፡፡እንዲሁም በ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአጠቃላይ 268 ሲሆኑ ስነምዕላድ 96 (36.5%) ስነአገባብ 86 (32.8%) ስነፍቺ 82(29.2%) ስነድምጽ 4(2%)ናቸው፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጻህፍቱና የመምህሩ መምሪያ በመርሀ-ትምህርቶቹ ይዘቶች ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ መሆናቸውን በመቶኛ ከተሰሉት ውጤቶች ተቀራራቢነት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተተኳ ሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን በተመለከተ በተደረገ ሰነድፍተሻ ተከታታይነትን በሚመለከት በመማሪያ

መጻህፍቱና የመምህሩ መምሪያ ውስጥ አብዛኛውን የድግግሞሽ መጠን የያዘው ስነምዕላድ ሲሆን 96 ( 37%) ስነአገባብ 86(31%) ስነፍቺ 84(16%) ስነድምጽ 4 (2%)ጊዜ ተደጋግመው ተደራጅተዋል፡፡ በመርሀ-ትምህርቶቹ ውስጥ ያለውን ድግግሞሽ ስንመለከት እንደ መማሪያ መጻህፍቱ እና መምህሩ መምሪያ ከፍተኛውን ቦታ የያዘው ስነ ምዕላድ ሲሆን 27(41%) ስነአገባብ 26(39.3%) ስነፍቺ 11(16፣7%) እንዲሁም ስነድምጽ 2(3%) ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች ተከታታይነት ያላቸው ሲሆን የድግግሞሽ መጠናቸው ግን ሚዛናዊነቱን የጠበቀ አይደለም፡፡ አንዳንድ የሰዋስው ይዘቶች በከፍተኛ መጠን ሲደጋገሙ አንዳንድ የሰዋስው ይዘቶች ደግሞ አንዴ ብቻ የቀረቡበትን ሁኔታ ለመመልከት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ተለጣጣቂነታቸውን በተመለከተ አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸው ሳይቋረጥ ከ7ኛ ክፍል ወደ ስምንተኛ ክፍል የተሸጋገሩ ቢሆንም በጣም ጥቂት ይዘቶች ግን ምንም ስፋትና ጥልቀታቸው ሳይጨምር የተደጋገሙ ናቸው፡፡ እንዲሁም እዛው ሰባተኛ ክፍል ላይ ብቻ የቀሩ እና 8ኛ ክፍል ላይ ብቻ የተካተቱ ይዘቶችም አሉ፡፡ በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን የተከተሉ ናቸው፡፡ በአመዛኙ ግን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ጎልቶ ታይባቸዋል፡፡

በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን በተመለከተ በተደረገ ሰነድፍተሻ በአብዛኛው ግልጽ፣ ትክክለኛነት የሚታይባቸው ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን ግልጽነት የጎደላቸው ማብራሪያዎች፣ ትእዛዞች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች እንዲሁም ስህተት ያለባቸው የሰዋስው ይዘቶች ታይተዋል፡፡ ሌላው ከተገቢነት አንጻር ከጥቂት ይዘቶች በስተቀር አብዛኞቹ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ይዘቶች እንደቀረቡ ከተደረገው ሰነድ ፍተሸ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከመመጣጠንም አንጻር ሁሉንም የሰዋስው ትምህርት ንኡሳን ይዘቶች ከስነድምጽ እስከ ስነፍቺ ያሉትን በአጠቃላይ የያዙ ቢሆንም ተመጣጣኝነታቸው ላይ ግን የሚዛናዊነት ችግር ይታያል፡፡ በተለይ ስነድምጽ በሁለቱም ክፍሎች ላይ ዝቀተኛ ሲሆን ስነምዕላድ ደግሞ ከፍተኛውን ቦታ ይዟል፡፡ ሌሎች የተቀሩት ግን ከሞላጎደል ተቀራራቢነት ያላቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ንኡሳን ይዘቶቹን አመጣጥኖ ከማቅረብ ረገድ ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በመሆኑም ከዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት መሰረት የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰጥተውታል፡፡

- *መማሪያ መጻህፍቱም ሆነ መምህሩ መምሪያ ሲዘጋጁ ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥኑ ተገቢ የሆኑ መልመጃዎችን ያካተቱ እንዲሆኑ ቢደረግ፤*
- የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ትክክለኛ ከስህተት የጸዱ እንዲሁም ግልጽና የማያሻሙ ሆነው እንዲቀርቡ ቢደረግ፤
- *መማሪያ መጻህፍቱም ሆነ መምህሩ መምሪያ ሲደራጁ የድግግሞሽ መጠናቸው ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆንና ተለጣጣቂነታቸውም ሳይቋረጥ ስፋትና ጥልቀቱ እየጨመረ እንዲቀጥል ቢደረግ፤*
- በ*መማሪያ መጻህፍቱም ሆነ* በመምህሩ *መምሪያ* ውስጥ የሚካተቱ ንኡሳን ይዘቶች ተመጣጥነው ቢቀርቡ ፤
- በተተኳሪዎቹ ሰነዶች ውስጥ የሚቀርቡት *መመሪያዎች*፣ ምሳሌዎች፣ *ማብራሪያዎች* እና መልመጃዎች ግልጽና ትክክለኛ እንዲሆኑ ቢደረግ፤
- *መማሪያ መጻህፍቱም ሆነ* የመምህሩ *መምሪያ* መርሀ-ትምህርቱን መሰረት አድርገው *መዘጋጀታቸው* የሚበረታታ ስለሆነ ቢቀጥል፤መርሀ-ትምህርቶቹም በ*ምዕራፍ* የተከፋፈሉና ግልጽ የሆኑ ይዘቶች ቢኖሯቸው፤
- በ*መማሪያ መጻህፍቱም ሆነ* በመምህሩ *መምሪያ* ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት በተመጣጠነ ሁኔታ ቢደራጁ
- ለ*መማሪያ መጻሕፍትና* ለመመህሩ *መምሪያ* አዘጋጆች ስልጠና ቢሰጥ፤
- ተተኳሪዎቹ ሰነዶች *ታትመው* ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት የሚመለከታቸው ባለሞ*ያዎችና* ልምድ ሳላቸው መምህራን በመስጠት እንዲገመግሙ ቢደረግ፤

# ዋቢ ጽሑፎች


ማረው ዓለሙ፡፡(1989)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ* ፡፡ አዲስ አበባ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰሚራ አሊ፡፡ (2010)፡፡ በደቡብ ክልል በ2014 ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ፡፡

ሽታዬ መኮንን፡፡ (2007)፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ከተቀመጠው ግብ አንጻር፤ ጉንችሬ መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2010)፡፡ *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡* (4ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ አልፋ አታሚዎች፡፡

ባዩ ተሾመ፡፡ (2004)፡፡ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ 2ኛ እርከን የአማርኛ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡ *ሥነ* ልሳንና ቋንቋ ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡

አበበች ገብሩ፡፡ (2004) ፡፡ ከ1998-2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ 2ኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

አተረፍ መዝገቡ፡፡ (2014)፡፡ ከ2005-2008 ዓ.ም ለ10ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች ከታላሚዎች መርሃ ትምህርቶችና መማሪያ መፃህፍት ጋር ያላቸው የይዘት ተዛምዶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ፡፡

እምሻው ማሞ። (2005)። ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል (ከ1998-2004 ዓ.ም) አማርኛ ቋንቋ *መማሪያ መጽሀፍ* ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

እስሌማን አባይ። (2003)። በ12ኛ ክፍል አማርኛ *መማሪያ መጽሀፍ* ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

ደመቀ ሙሉጌታ። (1989)። በደብረብርሀንና በደሴ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋዋሞች ለሚሰለጥኑ መምህራን የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ *መማሪያ* ማስተማሪያ *መጻህፉ* የመርሀትምህርቱን አላማዎች የሚያሟሉ ናቸው? በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

ጌታሁን አማረ። (2014)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ።* (15ኛ እትም) አዲስ አበባ፣አልፋ አታሚዎች።

Alderson, J. C. (1993). The Relationship between Grammar and Reading in English for Academic Purposes Test Battery. *In D. Douglas, & C. Chappelle (Eds.), A New Decade of Language Testing Research: Selected Papers from the 1990 Language Testing Research Colloquium.* Alexandria, VA: TESOL.

Atkinns, A. (2000). Pedagogical Grammer and Second Language Acquisition. Assessments Task.2

Azar, B. (2007). Grammar-Based Teaching: A Practitioner's Perspective. *TESL-EJ.* 11(2). 1-12 Retrieved January 12, 2021 from http://www.tesl-ej.org/ej42/a1.pdf

Batstone, R. (2012). Language form, task-based language teaching, and the classroom context, *ELT Journal, Volume 66, Issue 4, P459—467,* https://doi.org/10.1093/elt/ccs058

Billows, F.L. (1961) *The Techniques of Language Teaching*. London; Longman.

Bridge International Academic (2018). The Benefits of Detailed Teacher Guides. Retrieved January 17, 2021, from https://www.bridgeinternationalacademies.com/the-benefits-of-detailed-teacher-guides/

Brown, H.D. (1994). *Principle of language learning and teaching.* NewJersey: Prenties Hall Inc.

Brown, H.G. (2000).*Teaching by Principles An Interactive Approach to Language Pedagogy.* (2nd Ed).Longman: Pearson Education

Callison, D. (2003). Textbook. *School Library Media Activities Monthly*, *19*(98), 31-40

Chomsky, N. (1978). *Syntactic Structures*. New York: Molten Publishers

Cohen, L. Manion, L. &Morrison, K. (2007). *Research Methods in Education* (6th ed.). London:Routledge.

Creswell, J.W., & Plano Clark, V.L. (2011). *Designing and Conducting Mixed Research*. Thousand Oaks: CA: Sage Publication.

Donald, S.G, & Kneale, P.E. (2001). *Study Skills for Language Students. A practical guide*. Oxford: Oxford University press

Dubin, F and E. Olishtain (1986). Course design developing programme in materials for language learning.

Edge, J. (1993). Essentials of English Language Teaching. London: Longman

Ellis, R. (2002). Grammar teaching practice or consciousness-raising? In J. Richards & W. Renandya (Eds.), *Methodology in language teaching*: *An anthology of current practice* (pp. 167-174). Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (2006). Current Issues in the Teaching of Grammar: *An SLA Perspective. TESOL Quarterly. 40(1): 83-107.*

Emery, D., J. Kierzek, and P. Lindblom. *(1978). English Fundamentals, 6th ed*. New York: Macmillan.

ETP. (1994). Federal Democratic Republic Government of Ethiopia Education and Training Policy, Addis Ababa April, 1994 ST. George Printing Press.

Fraenkel, J.R. & Wallen, N.E. (2014). *How to design and evaluate education research* (7th ed). McGraw Hill, Higher education, Boston.

Gay, L.R, Geoffrey, E.M, & Airasian, P. (2012). *Educational research, competence for analysis and application* (10th ed), Pearson Boston.

Greenbaum, S (1996). *The Oxford Grammar*, Oxford, Oxford university press.

Greenbaum, S. (1982). What is grammar and why teach it? Unpublished manuscript.

Grossman, P., & Thompson, C. (2008). Learning from curriculum materials: Scaffolds for new teachers. *Teaching and Teacher Education*, *24*(8), 2014—2026. https://doi.org/10.1016/j.tate.2008.05.002

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. London: Longman

Hdfield, J. & Hdfield, C.(2008). *Introduction to Teaching English*. Oxford: Oxford University press

http://education:waikato.ac.nz/reseach/files/etpc/2006v5n1nar1.pdf

Hutchinson, T & A. Waters (1987). *English for specific purposes; learning centered approach*. Cambridge University Press.

Hutchinson, T., & Torres, E. (1994). The textbook as an agent of change. *English Language Teaching Journal, 48(4), 315-328.*

JeongAe Y, HyeSeung, L. & Cheryl, J.C. (2019). Remaking textbook policy: analysis of national curriculum alignment in Korean school textbooks, *Asia Pacific Journal of Education Volume 20, Issue 3, P1—17, https://doi.org/10.1080/02188791.2019.1572591*

Kohli, A.L.(1984). *Techniques of Teaching English*. Delhi: Dhanpat Rai & Sons. Print.

Larsen-Freeman, D. (2001). *Teaching Grammar. In M. Celce-Murcia (ed.), Teaching English as a Second or Foreign Language* (3rd ed., pp. 251-66). Boston, MA: Thomson/ Heinle.

McDonough, J.,& Shaw,C.(1993). *Materials & Methods in ELT.Ateachers Guide*. Oxford University Press.

Mulroy, D. (2003). *The war against grammar.* Portsmouth, NH: Boynton/Cook.Publishers, Inc

Nassaji, H. & Fotos, S. (2011). *Teaching grammar in second language classrooms:* Integrating form-focused instruction in communicative context. Routledge: New York.

Nelson, G. (2001). English an essential grammar. NewYork: Routledge.

Nunan, D. (1998). Teaching Grammar in Context. *ELT Journal 52(2): 101-109.*

*Nunan.D. (1988).Syllabus Design.Oxford OUP.*

Powell, J. C., & Anderson, R. D. (2002). Changing teachers' practice: Curriculum materials and science education reform in the USA. *Studies in Science Education, 37, 107-136.*

Quader, D. A. (2001). Reaction to innovation in language teaching:A project in Bangladesh. *Journal of the Institute of Modern Languages,* 5-20.

Richards, J. & Rodgers, T. (1986). *Approaches and Methods in Language Teaching.* Cambridge University press

Richards, J. & Rodgers, T. (2001). *Approaches and methods in language teaching* (2nd ed.). Cambridge: Cambridge University Press.kalimat bahasa Inggris. *Fenomena, 3*(2), 27-38.

Richards, J. & W. Renandya. (2002). *Methodology in Language Teaching*. USA: Cambridge University Press

Richards, J., Platt, J., & Platt, H. (1992). *Longman Dictionary of language teaching and applied linguistics*. London: Longman.

Richards, J.C (1986).The Context of Language Teaching. Newyork: Cambridge University Press.

Richards,J. (2006). *Communicative Language Teaching Today*. Cambridge university press: New York.

Sheldon, L.E. (1988)." Evaluating EL T Text Book and Materials." *ELT Journal. Vo1.42, NoA,237-246*

St. George, E. S. (2001). Textbooks as a vehicle for curriculum reform. *Unpublished doctoral dissertation*, Florida State University.

Stern, H.H. (1992). *Issues and Options in Language Teaching*. Oxford University Press

Swan, M. (1994). *Design Criteria for Pedagogical Language RUles*. In Bygate, M. 'etal.' (eds.), *Grammar and the Language Teacher*. (ppA5-55). New York: Prentice Hall.

Tabbert, R. (1984). Parsing the Question —Why Teach Grammar‖. *The English Journal*. 73(8): 38-42

Terrell, T.D. (1991). The Role of Grammar Instruction in a Communicative Approach. *The Modern Language Journal.* 75(1): 52-63. http://dx.doi.org/ 10.1111/j.1540-4781.1989.tb02537.x

Thornbury, S. (1999). *How to Teach Grammar. Essex*: Pearson Education Limited

Taylor, R. (2014). Basic Principles of Curriculum and Introduction. Chicago

University press

UNICEF (2015). ToT modules on inclusive education. Introductory module, modules13.NewYork: UNICEF. Available online e:http://www.inclusiveeducatin org/basic-p UNICEF icef-trainer-trainers-modules-inclusive-education

Ur, P. (2014). *Grammar practice activities (2nd ed.)*. Cambridge, UK: Cambridge University. Press

Ur, P. (1 A course *in Language Teaching*: Practice theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. (1999). *Grammar practice activities*: *A practical guide for teachers* (2nd ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Widodo, (2006). "Approach and procedures for teaching grammar." *Journal of ETP vol 5, No 1 pp.122-141.*

*Woods, E. (1995). Introduction Grammar.Lonndon: London press.*

Williams, D. (2005). *The Teacher's Grammar book*. (Second edition) Sako University.New Jersey: London